የፍትሀብሄር ክርክሮች ስርዓተ ችሎት

በፋሲል ወንድወሰን

እና

እሸቱ ያደታ

የስልጠናው ዓላማ

- ተሳታፊዎች በስልጠና ማብቂያ ላይ፤-
  - የፍትሀብሄር ክርክር/ሙግት አመራር ላይ የነበራቸውን ግንዛቤ ከፍ ያደርጋሉ
  - በፍትሀብሄር ስነስርዓት ህጉ እና አተገባበሩ ላይ ያሉ ጥያቄዎች ላይ በውይይት ይፈታሉ
  - በስራ ላይ እያጋጠሙ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት መፍትሄዎቻቸውን ያስቀምጣሉ
  - የፍትሀብሄር ክርክር በመምራትና በስርዓተ ችሎቱ ሂደት በተለየ ሁኔታ የሚያደርጉትን ጥንቃቄ ይመለከታሉ

1.የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ዓላማና ተግባር

* የፍትሀብሄር ህግ መብቶችና ግዴታዎች ባጠቃላይ የመሰረታዊ ህግጋት (substantive laws) ማስፈጸሚያና ማስተግበሪያ የህግ ማዕቀፍ ነው።
* የፍትሀብሄር ሙግት/ክርክር ከመነሻው እስከ ፍጻሜው የሚመራበት ቅደምተከተልና ሂደት (process)ነው።
* **መወያያ**፤በስነስርዓት ህግ ምክንያት መሰረታዊ መብቶች ሊጣሱና ሊታለፉ አይገባም ሲባል አፈጻጸሙ እንዴት ሊታይ ይገባል (የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 199 ይመልከቱ)ቅጽ 22 መ/ቁ 138479

የቀጠለ.....

* 1/ተከራካሪዎችን በፍትሃዊነት ስርዓት በስነስርዓቱ አግባብ በእኩልነት መርህ የማስተናገድ (Due Process/minimum standard of fair trial)ቅጽ 12 መ/ቁ 52546 ቅጽ 6 መ/ቁ 25026፤ ቅጽ 8 መ/ቁ 37761
* መገለጫዎቹም 1. ለተከራካሪዎች በቂና ሚዛናዊ ጊዜ መስጠት ለጽሁፍ ዝግጅት ለክርክር
* 2.በጠበቃ የመታገዝ መብታቸውን ማክበር 197(4)
* 3.ግራ ቀኙ የጽሁፍና የቃል ክርክር ለማድረግ ማስረጃዎቻቸውንም በአግባቡ እንዲያቀርቡ የማድረግ
* 4.ተከራካሪዎችን በእኩልነት መርህ ማስተናገድ
* 5.በራስ ጉዳይ/በልዩ ሁኔታ በሚያውቁት ጉዳይ ዳኛ ያለመሆንና ራስን ከችሎት ማንሳት

የቀጠለ.....

* 2/ሙግቶችን ወጪ ቆጣቢና ተከራካሪዎችንም ሆነ ፍ/ቤቱን እንዲሁም 3ኛ ወገኖችን ካልተፈለገ ወጪ መጠበቅ (efficiency/economic)
* 3/የተፋጠነ ፍትህ ለማሰጠት(expedient disposal)
* Justice delayed is justice denied/justice rushed is justice crushed(የዘገየ ፍትህ እንደተከለከለ ይቆጠራል/የተዋከበ የፍርድ ሂደት ፍርደ ገምድል ይሆናል)

የስነስርዓት አወቃቀር ሞዴል

1/የአንግሎ ሳክሰን ሞዴል(Common Law/Adversarial Model)

- ክርክሩንም ሆነ ማስረጃ በመስማት የሚመሩት ባለጉዳዮቹ ተከራካሪዎቹ ናቸው።
- የዳኛው ሚና ችሎት ከማስከበር የዘለለ አይደለም።(passive role)
- እውነት ስለመውጣት አለመውጣቱ ግድ አይሰጠውም።የበለጠ ለሞገተና ላስረዳው ፍርዱ ይሰጣል።

2/የሲቪል ሞዴል(Civil Law/Inqusitorial Model)

- የክርክሩን መሪና ተቆጣጣሪ ዳኛው ነው።(Active role)
- እውነቱን ለማውጣት ጥረት ያደርጋል።(በክስ መስማቱም ሆነ በምስክር መስማት ዋነኛ ሚናው የዳኛው ነው) ቅጽ 24 መ/ቁ 168094
- እውነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ወይም ወደ እውነቱ በተጠጋ ማስረጃ ምዘና ፍትህ የተመላበት ውሳኔ ይሰጣል።

የፍ/ቤቶችን/ዳኝነት አካሉን ስልጣን ስለመለየት አዋጅ 1234/13

ብሄራዊ ስልጣን ቅጽ 21 መ/ቁ 183200

የስረነገር ስልጣን

- ባመዛኙ በአለም አቀፍ የዳበሩ የህግ ትርጉሞች የሚመራ ይሆናል
- ከአገራዊ ግዛት ጋር ንክኪ ያለው መሆኑን መመልከት(foreign element)
- በባለጉዳዮቹ ማንነትና በንብረቱ መቼት በፍርዱ አፈጻጸም ሁኔታ ላይ ይመሰረታል
- ቅጽ 18 መ/ቁ 100290

- የትኛው የዳኝነት አካል ስልጣን ነው; እንዲሁም የትኛው አስተዳደራዊ አካል ዳኝነት ስልጣን ስር ይወድቃል የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል
- የፌዴራሉ የአስተዳደሩ ወይም የማህበራዊ ፍ/ቤት ስልጣን የሚለውን መመርመር

የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን 1234/13 አንቀጽ 5 ስ/ስ 9፤ 244(2)

* 1. የክርክሩ መነሻ የሆነውን የህግ ማዕቀፍ መመልከት(የፊደራል ህጎችን መሰረት አድርገው የሚነሱ ክርክሮች)
* 2. የተከራካሪዎችን ማንነትና ነዋሪነት መመልከት(የውጭ አገር ዜጎች ቅጽ 5 መ/ቁ 28883 ቅጽ 10 መ/ቁ 42928፤በተለያየ ክልል ነዋሪ የሐኑ ቅጽ 8 መ/ቁ 36460፤በፊዴራል መንግስት የተመዘገቡ ተቀማት ቅጽ 10 መ/ቁ 43912 ቅጽ 18 መ/ቁ 97083 ፤የፊዴራል መንግስቱ አካላት
* 3.የክሱ ሰረነገር በአዲስአበባ ወይም ድሬዳዋ ላይ መከሰት
* 4. በጉዳዩ ዓይነት ተለይቶ ለፊዴራል ፍ/ቤቶች ወይም ለክልሉ ፍ/ቤቶች የተሰጡ መሆንን መመልከት

የቀጠለ

- የክርክር ግምትን መሰረት ያደረገ መሆኑ ክርክሮች በተቻለ መጠን ተገምተው መቅረብ አለባቸው ስ/ስ/226-228 ተገምተው መቅረብ ለማይችሉ ጉዳዮች ከዜግነት ጉዳይ በቀር እና አለምአቀፍ የግለሰብ ህግን ተመስርቶ ከሚነሱ ጉዳዮች በቀር ቅጽ 18 መ/ቁ 100290
- መወያያ ግምታቸው የፈለገውን መጠን ቢሆንም በመጀመሪያ ደረጃ የሚታዩ ጉዳዮች ስራ ክርክር ቤተሰብ የንብረት ማጣራት ጉዳዮች
- አንዳንድ ክልሎች የፌዴራል ጉዳይን በውክልና የመዳኘት ስልጣን መነሳት ቅጽ 6 መ/ቁ 20645 አዋጅ 322/95

ሌሎች አካላት

* የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ቦርድ የወል የስራ ክርክርን በተመለከተ
* አዋጅ 1156/11
* የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደራዊ ፍ/ቤትን በተመለከተ
* የማህበራዊ ፍ/ቤትን በተመለከተ አዋጅ 3/2000 ድህነት ማስረጃ መስጠት አንቀጽ 14(4)እና እስከ ብር 2000 ፍትሀብሄር ፍ/ብ/ህ/ቁ 1212-1221 ፤1245፤1246 ንግድወረቀቶች አይምሮ ንብረት ኢንሹራንስ
* የግብር ጉዳዮችን በተመለከተ አቤቱታ አጣሪ እና ግብር ይግባኝ
* ያልተገባ የንግድ ውድድርና ንግድ ምልክት የንግድ አሰራር አጣሪ ኮሚሽን ቅጽ 12 መ/ቁ 45682፤ 55162 አዋጅ 501/98 ቁ. 49 አዋጅ 329/95
* የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉባዔን በተመለከተ አዋጅ 1161/11
* የሽሪዓ ፍ/ቤቶችን በተመለከተ አዋጅ 188/91
* ጡረታን የተመለከቱ የማህበራዊ ዋስትና ጉዳዮች

በፍርድ የማያልቁ ጉዳዮች/Non-justiciable matters ፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 231

* በመርህ ደረጃ በግልጽ ለዚህ አካል የመዳኘት ኃላፊነቱ ተሰጥቷል ተብሎ በልዩ ህግ እስካልተመለከተ ድረስ በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ የፍትሀብሄር ጉዳዮች የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ነው ስ/ስ/ 4 ቅጽ 21 መ/ቁ 136775፤ ቅጽ 15 መ/ቁ 80202

1. ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ህገመንግስት አንቀጽ 11 የመንግስትና የሀይማኖት መነጣጠል ቅጽ 18 መ/ቁ 97007፤ ቅጽ 13 መ/ቁ 66957፤ ቅጽ 14 መ/ቁ 77479፤ ቅጽ 9 መ/ቁ 34440

2.ፖለቲካዊ እና ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች፤ የም/ቤት አባላትን፤ የካቢኔ አባላትን፤ የተሸ ሚዎች ፖሊስ፤ ዐቃቤህግ፤ መከላከያ፤ ዳኞች ጉዳይ ቅጽ 12 መ/ቁ 63417

3. አለምአቀፍ ከለላ ያላቸው ግለሰቦች እና ተቃማት ቅጽ 19 መ/ቁ 117390፤ ቅጽ 17 መ/ቁ 98541

የቀጠለ....

* 4. አስተዳደራዊ ጉዳዮች አዋጅ ቁጥር 1183/12 በፍርድ ክለሳ መመልከት አስተዳደራዊ ሂደቶችን ደረጃ በደረጃ ከጨረሱ በሃላ ወይም ያለተገባ መዘግየት ካጋጠመ፤ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ወይም መመሪያዎች ድጋሚ ይከለሱልን ይሰረዙልን ዳኝነቶች ካልሆኑ በቀጥታ ለፍ/ቤት ለመቅረብ አይችሉም፤ ቅጽ 20 መ/ቁ 119704
* 5. የሰብዓዊ መብቶች ዳኝነት ማህበራዊ ምጣኔሀብታዊ ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ መብቶች አዋጅ 1234/13 አንቀጽ 11(3) በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ እና የማይቻሉት የትኞቹ ናቸው ፤ ሊፈጸሙ የሚችሉት የማይችሉት፤ ደረጃ በደረጃ የሚፈጸሙት የሀገሪቱ ኤኮኖሚ የሚፈቅዳቸው progressive realization
* 6 constitutional interpretation ህገመንግስትን የመተርጎም ጉዳዮች ቅጽ 14 መ/ቁ 43511

የግዛት/አጥቢያ/አካባቢ ስልጣን ስ/ስ/10፤19-31

* ለሙግቱ አመራር አመቺውን ችሎት ስለመምረጥ
* ቅጽ 10 መ/ቁ 48018 ለውል ውጪ ጉዳይቅጽ 7 መ/ቁ 34076 ለውርስ ጉዳይ
* ጥብቅ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም ቅጽ 19 መ/ቁ 109383 ትክክለኛ ፍትህ ሊያሰጡ አያሥችሉም ከሚባሉ ምክንያቶች በቀር ስ/ስ/ 31
* በተለያየ ችሎት መዝገብ በተመሳሳይ ጉዳይ ከተከፈተ እንዲጣመር መጠየቅ ስ/ስ 11 ቅጽ 15 መ/ቁ 81275
* የፍ/ቤት ስልጣን የሚወሰነው ሙሉ ክሱ ይዘቱና የሚጠየቀው ዳኝነት ጭምር ታይቶ እንጂ ርዕሰ ብቻ በማየት ሊሆን አይችልም ቅጽ 18 መ/ቁ 102543፤ ቅጽ 11 መ/ቁ 49985
* መወያያ አንድ ፍ/ቤት ሳልጣን ሳይኖረው የሰጠው ፍርድ እስካልተሸረ ድረስ የጸና ነው ወይስ ከጅምሩ ውጤት አልባ ፍርስ ነው፤ አዋጅ 1234/13 አንቀጽ 51(1) ቅጽ 21 መ/ቁ 100295፤ ቅጽ 13 መ/ቁ 73696፤ ቅጽ 18 መ/ቁ 101345፤ ቅጽ 15 መ/ቁ 85718 ቅጽ 6 መ/ቁ 32229

ክስ ከመሰማቱ በፊት ያሉ ሂደቶች

* የክስ ማመልከቻን ስለመመርመር (pleading Stage)
* በፍርድ ኦፊሰር ወይም ሬጅስትረር ደረጃ ስለመመርመር ፍ/ስ 80-93 እና 222-228 በተለይ የፍ/ስ/ 222፤223፤238 እና 92፤93 መሰረት መቅረቡን" ኮፒ ሰነዶች ከዋናው ጋር መገናዘባቸውን/መመሳከራቸውን ቅጽ 20 መ/ቁ 125699
* በዳኞች ስለመመርመር 229-232 በተለይም የፍ/ቤቱ ስልጣን መሆን ያለመሆኑን (Jurisdiction) እንዲሁም ጉዳዩ በፍርድ ሊያልቅ የሚችልና የክስ ምክንያት (Justiciability & Cause of Action) ያለው መሆን ያለመሆኑን ፍ/ስ/ 4 ቅጽ 6 መ/ቁ 23608፤ቅጽ 15 መ/ቁ 80202
* ከለላ ያላቸውን ተቀ□ማት መለየት ቅጽ 19 መ/ቁ 117390
* በፍርድ የማያልቁ ጉዳዮች ሀይማኖታዊ ጉዳዮች መ/ቁ 97007፤34440፤66957፤77479
* በግልግል የሚያልቁ ጉዳዮች ቅጽ 17 መ/ቁ 106286 ቅጽ 24 መ/ቁ 161062 አዋጅ ቁጥር 1237/13

የባለጉዳዮች ችሎታ እና መብትና ጥቅም ስ/ስ/ 3334

* ችሎታ ሳይኖር ክርክር ማድረግ ፍርዱ ውጤት አይኖረውም ቅጽ 17 መ/ቁ 103781 ቅጽ 11 መ/ቁ 55794
* መብትና ጥቅም ሰበር 15270፤22719፤23769፤48699፤45161፤ 36320
* ተከራካሪን ስለመጨመር ስለመተካት ስ/ስ/ 40፤39 ሰበር 43424፤ 39540፤37725፤34249

የክስ ምክንያት ቅጽ 21 መ/ቁ 136775

* የካርታ አሰጣጥ ስረዛ ክልከላ ህግን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑ በፍ/ቤት ዳኝነት ሊታዩ ይችላሉ ሰበር ቅጽ 13 መ/ቁ 57186፤ 67631፤64014 ቅጽ 14 መ/ቁ 75414 ቅጽ 18 መ/ቁ 99071
* መህንድስናን መሰረት ያደረጉ ዳኝነቶች ግን በፍርድ የሚያልቁ አይደሉም ቅጽ 3 መ/ቁ 14554 31906 እና ቅጽ 9 መ/ቁ 39529
* በመንግስት የተያዙ ቤቶች ጋር በመፋለም ማቅረቡ ይሻላል 47/67
* የባዶ መሬት ውልን የተመለከቱ ክርክሮች ቅጽ 6 መ/ቁ 27739 ቅጽ 18 መ/ቁ 100671
* ሰራ ቀዋሚ ልደረግ
* ስም ዝውውር ያድርጉልኝ ቅጽ 15 መ/ቁ 82234 ቅጽ 7 መ/ቁ 18380 ቅጽ 12 መ/ቁ 56386
* ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት ላይ ፍቺ ይወሰንልኝ
* ውል ኑዛዜ ይጽደቅልኝ ቅጽ 7 መ/ቁ 18380

የቀጠለ

- ዳኝነትና (የህግ ማስታወቂያ 177/45) ዳኝነት በመብቱ ልክ ከከፈለ በቂ ነው የፍ/ቤቱም ስልጣን የሚወሰነው በከሳሹ ድርሻ ልክ ብቻ ነው ቅጽ 24 መ/ቁ 167589
- የቴምብር ቀረጥ መክፈሉን (አዋጅ ቁ. 110/90) ወይም በአግባቡ በመታለ ቃል ተደግፎ የቀረበ የድህነት አቤቱታ ተደግፎ መቅረቡን ፍ/ስ 205፤468 ድርጅቶችም የድህነት አቤቱታ ርቡ ይችላሉ ቅጽ 22 መ/ቁ 121938
- አቤቱታው በሚመለከተው ባለጉዳይ በራሱ፤ በቤተሰብ ውክልና ፍ/ስ/58 ቅጽ 20 መ/ቁ 117803 እና 102141 ቅጽ 16 መ/ቁ 91493 94302 ቅጽ 21 መ/ቁ 131622 ወይም ጠበቃ ፍ/ስ/63 ወይም ወኪል/ነገረፈጅ
- በክርክር ሂደት ከሞቱ መተካት ስ/ስ 48 49 በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ቅጽ 13 መቁ 62452 ቅጽ 18 መ/ቁ 105626
- በሞተ ሰው ውክልና መክራከር ፍርዱ ውጤት የለውም ቅጽ 17 መ/ቁ 95587

የክስና መልስ ዝግጅት

* የተማላ ፍሬ ጉዳይና ማስረጃ መያዙ ቅጽ 16 መ/ቁ 91329 ቅጽ 15 መ/ቁ 77983፤83915 የክሱን ስረነገር የጉዳዩን መሰረት
* የሚጠየቀው ዳኝነት ግልጽነት
* ከየትኛው ተከሳሽ ምን ዳኝነት እንደሚጠየቅ
* በመልስደረጃ ሁሌም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ካሉ አለመዘንጋት
* በግልጽ መካድ 83፤ 235 ቅጽ 9 መ/ቁ 48632፤ ቅጽ 19 መ/ቁ 109206 እና 104028፤ የካሳ መጠንን በተመለከተ ተከሳሽ በዝምታ ማለፉ እንዳመነ አያስቆጥረውም መጠኑ በማስረጃ መረጋገጥ አለበት ቅጽ 18 መ/ቁ 111599
* የተከሳሽከሳሽነት ካለ በመልሱ አካቶ ፣ማቅረብ 234(1)(ረ) በዚያው ከሳሽ ላይ የተወሰነ ከሆነ ብቻ ቅጽ 21 መ/ቁ 102668፤ ቅጽ 17 መ/ቁ 94713 ስልጣኑ ካልሆነ መዝገቡን በሙሉ ማስተላለፍ ቅጽ 15 83169
* ተገቢውን ዳኝነት ማስከፈል ቅጽ 15 መ/ቁ 86454

መጥሪያ አደራረስ ፍ/ስ/94-110፤233

- የመሰማት መብት መርሆ ነው።
- መጥሪያ ከክሱና ማስረጃው ጋር ተሟልቶ ለተጠሪው/ተከሳሽ ይላካል። ክሱ ከተሸሻለም በድጋሚ መጥሪያ መድረስ አለበት ቅጽ 19 መ/ቁ 107838
- በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል። ቢያንስ 10 ቀን ቀድሞ ፍ/ስ 240 ሰበር ቅጽ 23 መ/ቁ 154727ለመልስ ማያያዝና ለክስ መስማቱ ቀኑ መደራረብ የለበትም። ቅጽ 8 መ/ቁ 36380
- በክስ መስማቱ ዕለት የግራ ቀኙ መቅረብ መረጋገጥ አለበት
- ግራ ቀኙ ለክስ መስማቱ ካልቀረቡ መዝገቡን መዝጋት(strike out) አለበት።ቅጽ 9 መ/ቁ 43410 ፍ/ስ/ 69(2)ቅጽ 22 መ/ቁ 136901
- ተሟልተው ካልቀረቡና ተከሳሹ ከቀረ መጥሪያ በአግባቡ የደረሰው ስለመሆን አለመሆኑ መጣራት አለበት።ፍ/ስ/ 70

የቀጠለ.....

- መጥሪያው በትክክል ካልደረሰ ወይም አጠራጣሪ ነገር ካለ ድጋሚ መጥሪያው እንዲደርስ ትዕዛዝ መስጠት በተለይ ለተቋማት የሚላኩ መጥሪያዎች **ለመዝገብ ቤት መስጠት በቂ አይደ**ለም ቅጽ 18 መ/ቁ 100673
- መጥሪያው ከደረሰ ማረጋገጫው በመኃላ ቃል ተደግፎ በምስክሮች ስም ተዘርዝሮ ስለአደራረሱ ሁኔታ ተረጋግጦ መቅረቡን ማረጋገጥ ፍ/ስ/ 102፤104፤205
- መጥሪያውን ለወኪሎች/ለቤተሰብ አባሎች ለማድረስ ይቻላል ፍ/ስ/ 96-101
- መጥሪያው ለማድረስ ያልተቻለ እንደሆነ እንዲሁም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ የተደረገውን ትጋት በማረጋገጥና በመዘርዘር በመኃላ ቃል በተደገፈ አቤቱታና በምስክሮች ስም ጭምር ማረጋገጥ ፍ/ስ 103/110፤205
- እንዳስፈላጊነቱ ምትክ መጥሪያ ማዘዝ ፍ/ስ/ 105-108፤109 አድራሻው ከተለየ በመ/ቤቱ በኩል፤በቀበሌው ወይም ፖሊስ በኩል፤በፖስታ ቤት በኩል፤ወይም እንዲለጠፍ ማዘዝ በግልጽ አደባባዮች፤በቀበሌዎች፤ጣቢያዎች፤
- ወይም በተደራሽ ጋዜጣ ጥሪ ማድረግ ሚዛናዊ ጊዜ ውስጥ

የቀጠለ.....

- ጋዜጣ ጥሪ አድራሻው ላልታወቀ ወይም በአድራሻው ሊገኝ ላልተቻለው ብቻ ነው።ቅጽ 9 መ/ቁ 50376፤50022፤ቅጽ 12 መ/ቁ 53113፤ቅጽ 3 መ/ቁ 16301 ከዚህ ሁሉ በኋላ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል።(*exparte*)
- ተጠሪው በቀጣይ ቀነ ቀጠሮ ከቀረበና በባለፈው የክስ መስማት ቀጠሮ የቀረው በበቂ ምክንያት መሆኑን በመኃላ ቃል ካረጋገጠ ወደ ክርክሩ ገብቶ ክርክሩ ካቆመበት ሊቀጥል ይችላል; 72 ካልሆነ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል። መልስ ካቀረበ በማናቸውም ክርክር ተመልሶ መቀጠል ይችላል 206006 ጥር 25/2014 ፤ 43731፤ 15835
- ካልሆነ ግን በሌለበት የተባለው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ እንዲነሳለት በፍ/ስ 78 መሰረት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።አቤቱታው በክስ መስማቱ ዕለት ያልቀረበው መጥሪያው በአግባቡ ያልደረሰው መሆኑን ወይም በበቂ ምክንያት/አክል መሆኑን በሚያመለክት ማስረጃ የተደገፈና ውሳኔው /ትዕዛዙ መሰጠቱን ካወቀበት በ 30 ቀናት ውስጥ ሊሆን ይገባዋል። ቅጽ 23 መ/ቁ 137704
- ሰበር ቅጽ 12 54080፤55078፤61846፤ሌሎች 50376፤90452፤ 76601፤100673፤101478፤35403፤43731፤14974

የቀጠለ.....

* ተጠሪው/ተከሳሽ የመከላከያ መልሱን መልስ ለመቀባበል/ለመለዋወጥ በተቀጠረ ቀን ካልቀረበና መልሱን ካላቀረበ መልስ የመስጠት መብቱን ከማጣት በቀር በሌለበት ይታይ ሊባል አይገባም። ቅጽ 6 መ/ቁ 24775/24111
* ፍ/ቤቱ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ የሰጠውን ትዕዛዝ/ውሳኔ ያነሳው እንደሆነ ሙግቱ እንደገና ይጀመራል፤ ተገቢነት ያለው ኪሳራም ለሌሎች ተከራካሪዎች እንዲቆረጥ ይታዘዛል
* ከሳሹ በክስ መስማቱ ለተያዘው ቀነ ቀጠሮ ካልቀረበና ተከሳሹ ካመነለት ፍርድ ይሰጣል፤ተከሳሹ ክሱን ሙሉ በሙሉ የካደ እንደሆነ ክሱ ይሰረዛል። (dismissal)ፍ/ስ/ 73 ከሳሽ የቀረበትን ቀን በበቂ ምክንያት በመታለ ቃል አስደግፎ ካቀረበ ኪሳራ ከፍሎ መዝገቡ በድጋሚ ሊንቀሳቀስ ይችላል።ፍ/ስ 74 ካልተፈቀደለት ግን በድጋሚ በዚሁ ጉዳይ ክስ የማቅረብ መብቱን ያጣል።

የቀጠለ.....

* መወያያ፡በድጋሚ ክስ የማቅረብ ያጣል ማለት በፍቺ፤ቀለብ፤ሞግዚትነት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አለው?
* መወያያ፡የጠበቃ/ነገረፈጅ መቅረት በቂ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል;
* መወያያ፡ ግራቀኙ ለክስ መስማቱ በተቀጠረው ቀነ ቀጠሮ በቀሩበት ቀን መዝገቡ ቢዘጋ ውጤቱ ምን ይሆናል፤
* መወያያ፤አንድ ፍ/ቤት በተለይ የስረነገር ስልጣን ሳይኖረው የተሰጠ ፍርድ ውጤቱ ምን ይሆናል;ቅጽ 6 መ/ቁ 32229፤ቅጽ 12 መ/ቁ 64703ቅጽ 17 መ/ቁ 98541፤ቅጽ 18 መ/ቁ 101345፤ቅጽ 15 መ/ቁ 85718
* መወያያ፤ተገቢውን ውክልና ሳይቀርብ የተደረገ ክርክር ወይም የቀረበ ክስና መልስ ውጤቱ ምን ይሆናል፤በተለይም በሞተ ሰው ውክልና መከራከር፤ቅጽ 18 መ/ቁ 95587፤ቅጽ 16 መ/ቁ 91493፤መ/ቁ 94302
* መወያያ፤በፍ/ስ/ 240 ላይ የተመለከተው 10 ቀን ምንን የተመለከተ ነው;

የጽሁፍ ማስረጃ ስለሚቀርብበት ሁኔታ

- የጽሁፍ ማስረጃዎችና የምስክሮች ስም ዝርዝር በተቻለ መጠን በክስና መልስ ማቅረብ ወቅት ተሟልተው መቅረብ አለባቸው።ፍ/ስ/ 223፤234
- በአቤቱታ ላይ ተሟልተው ሳይቀርቡ የቀሩ ማስረጃዎች በክስ መስማት ለተያዘው ቀነ ቀጠሮ ሊቀርቡ ይችላሉ ፍ/ስ/ 137(1)ቅጽ 24 መ/ቁ 160314 ያኛው ወገን አስተያየት መስጠትና ማስረጃውን በክርክር የመሞገት መብት አለው
- በነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ሳይቀርቡ የቀሩት ማስረጃዎች በከባድና በበቂ ምክንያቶች የሆነ እንደሆነ በመታለ ቃል ተደግፎ ሲቀርብ 205፤256 መሰረት በተለየና በጥብቅ ሁኔታ ሊፈቀድ ይቻላል።
- ነገር ግን ፍ/ቤቶች ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲሉ በተከራካሪ ወገኖች ያልቀረቡ ማስረጃዎች ቢሆኑም አስቀርበው መመርመር ይችላሉ።ፍ/ስ/ 249 እና 264
- ባለጉዳዮች በፍ/ስ 145 ይቅረቡልን የሚለ ቸው ማስረጃዎች

የ 3ኛ ወገኖች ጣልቃገብነት ወይም ክስ ውስጥ መግባት ፍ/ስ/41 ፤43

- በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ስላለው ክርክር መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው በአቤቱታው ይህንን አስመልክቶ ጣልቃ ለመግባት ማስፈቀጃ በማቅረብ ፍ/ቤቱም የጣልቃገብ አመልካቹን አቤቱታ በመመርምር ራሱን በቻለ ሌላ መዝገብ ሊታይ የማይቻልና በተያዘው ክርክር ዕልባት ሊሰጠው የሚገባ መብቱን የሚያመላክት ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ ጣልቃገቡ ወደክርክሩ እንዲገባ ሊፈቅድለት ይችላል። ቅጽ 16 መ/ቁ 95934 ሰነድ ማስረጃ አላቀረበክም ተብሎ ጣልቃመግባት አይከለከልም ቅጽ 17 መ/ቁ 90713
- መወያያ፡ጣልቃ የመግባት ስነስርዓት በምን መልኩ ይፈጸማል;ቅድመ ሁኔታዎቹ ምንድን ናቸው፤ የከሳሽ ወይስ የተከሳሽ ሚና ይኖረዋል;በማን ዘንግ ነው የሚከራከረው ዳኝነትስ ይከፍላል፡

የቀጠለ.....

- በተመሳሳይ በተከሳሹ ጠያቂነት በዕዳነት የሚመለከተው ወይም የክሱ የመጨረሻ ኃላፊነት ያርፍበታል የሚባለው 3ኛ ወገን ወደ ክሱ ይግባልኝ ተብሎ ሲያመልክትና የኃላፊነቱንም ዓይነትና ወሰን የሚያመለክት ማስረጃ ሲያቀርብ ፍ/ቤቱ ወደ ክርክሩ እንዲገባና መጥሪያ እንዲደርሰው ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።ፍ/ስ/ 43
- ነገር ግን ገብቶ መመ□ገት የሚችለው ከከሳሽ ሸገር እንጂ የጎንዮሽ ከተከሳሽ ጋር ከሆነ መሰናበትና በራሳቸው በሌላ አዲስ መዝገብ ይከራከሩ ቅጽ 14 መ/ቁ 79465
- እንዲሁም ፍ/ቤቱ በከሳሽነት ወይም ተከሳሽነት ሊካተት የሚገባው ያልተጣመረ ወገን እንዳለ ሲረዳ ወይም ያላግባብ የተጣመረ ወይም የተካተተ ወገን መኖሩን ሲረዳው ትክክለኛው ተከራካሪ እንዲገባና የማይመለከተው እንዲሰናበት ተገቢነት ያለውን ትዕዛዝ ይሰጣል።ፍ/ስ/ 39፤40
- ጣልቃገብ የተፈቀደለትና የገባ ወገን መግባቱ ተገቢ ያለመሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ሊሰናበት ይችላል። ቅጽ 23 መ/ቁ 144470
- ጣልቃገብ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካለው ማንሳት መብቱ ነው ቅጽ 22 መ/ቁ 135254

አቤቱታ ስለማሻሻል 91

* ተከራካሪ ወገኖች በአቤቱታ አጻጻፍ ጉድለት ብቻ ፍትህን ሊያጡ አይገባም።
* በመሆኑም በፍ/ቤቱ አነሳሽነት (አቤቱታው ግልጽነት የጎደለው ከሆነ ወይም ጸያፍ አገላለጾችን የተጠቀመ ከሆነ ሊብራሩ የሚገባቸው ነጥቦች ሳይብራሩ የቀረቡበት እንደሆነ) ቅጽ 20 መ/ቁ 122249 ወይም በተከራካሪው ወገን ጠያቂነት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሊያግዙ የሚችሉ ነጥቦች ያሉ እንደሆነ አቤቱታው እንዲሻሻል ሊፈቀድ ይችላል።
* የአቤቱታ መሻሻል የክሱን ስረነገር ወይም ምክንያት ሳይለውጡ መሆን ይገባዋል።ቅጽ 19 መ/ቁ 100475 ፤ በሌላ የክስ ምክንያት መተካት ሊፈቀድ አይገባም ቅጽ 24 መ/ቁ 161736 ክስ ማሻሻል ማለት ያልተገለጹ ፍሬ ጉዳዮችን አብራርቶና ገልጾ ማቅረብ ያልተጠየቁ ዳኝነቶችን አሟልቶ ማቅረብ፤ያልተሟሉ ማስረጃዎችን ማቅረብ
* አቤቱታን ማሻሻል ሌላውን ወገን ለኪሳራ ሊዳርግ ስለሚችል ኪሳራ ሊቆረጥ ይገባል
* በቀድሞው የመከላከያ መልስ ያልተካተተ የይርጋ መቃወሚያ በማሻሻል ሽፋን ሊነሳ አይቻልም። ቅጽ 12 መ/ቁ 55973

የቀጠለ

- አቤቱታ ሲሻሻል ከተፈቀደበት ነጥብ ውጪ ከሆነ በድጋሚ እንዲያርም ሚድረግ ያስፈልጋል ሲፈቀድ ከጅምሩ ማሻሻያ ነጥቦቹን ፍ/ቤቱ መለየት አለበት ቅጽ 22 መ/ቁ 104621
- በክስ መሻሻል ፍ/ስ/ 91(5) እንዲሁም በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ግምት ከፍተኛነት መነሻ ፍ/ቤቱ ስልጣኑን ካጣ ወይም በግምት መለወጥ የተነሳ ፍ/ስ/ 250 ስልጣኑ ለሆነው ፍ/ቤት ማስተላለፍ አለበት ቅጽ 24 መ/ቁ 173416
- ነገር ግን ክርክሩ ተጀምሮ በኢኮኖሚያዊ መለዋወጥ የተነሳ ግምት ከፍ ዝቅ ማለት የፍ/ቤቱን ስልጣን አይለውጠውም ፍ/ስ/ 16(4)
- ፍ/ቤቱም ግልጽነት በጎደለውና ትክክል ባልሆነ አቤቱታ እንዲሻሻል ትዕዛዝ ሳይሰጥ የሚሰጠው ፍርድ አግባብ ባለመሆኑ የበላይ ፍ/ቤት እንዲሻሻልና የመሰለውን እንዲወስን ሊመልስለት ይችላል ቅጽ 12 መ/ቁ 63699

ክስ መስማት/ተከራካሪዎችን ስለመመርመር

- ክስ መስማት የዳኛው ሚና ጎልቶ የሚወጣበት ነው፤ለክስ መስማቱ ሂደት በሚያስፈልገው መጠን መዝገቡን አጥንቶና አከራካሪ ነጥቦችን ለይቶ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት፤፤ በ 145 የሚቀርቡትንም በሙሉ አስቀርቦ ቅጽ 15 መ/ቁ 89494 ፤85466
- ክስ መስማት ማለት በጽሁፍ ያስገቡትን ክስና መልስ ደግሞ ማንበብ አይደለም
- በክስ መስማት ዕለት ፍ/ቤቱ የቀረበውን ወገን ይመረምራል፤የመመርመር ስልጣኑም የፍ/ቤቱ ነው፡፡ተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ካላቸው በፍ/ቤቱ በኩል እንዲጠየቅላቸው ማድረግ ይችላሉ፡፡241/2
- በጽሁፍ ከጠየቀው ውጪ አዲስ ነገር ማንሳት አይችልም ቅጽ 15 መ/ቁ 86510

የቀጠለ.....

የታመነና የተካደ (አከራካሪ ነጥቦች) ፍሬ ጉዳይ ተለይተው የሚታወቀው በዚህ ሂደት ነው።በታመነው ጉዳይ ላይ ወዲያውኑ ከፊል ፍርድ ይሰጣል ፍ/ስ/ 242፤83፤235 ቅጽ 22 መ/ቁ 138717 ቅጽ 21 መ/ቁ 124669 ቅጽ 19 መ/ቁ 112927 .Q.በጽሁፍ መልሱ አምኖ በክስ መስማቱ ቢክድስ ፍ/ስ 90

- በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ አከራክሮ ብይን ይሰጣል ፍ/ስ/244፤245 መቃወሚያዎች በ244 ስር የተወሰኑ አይደሉም።
- መቃወሚያዎች በጽሁፍ መልስ ተጠቃለው መቅረብ አለባቸው ቢዘገይ በክስ መስማት ዕለት መቅረብ አለባቸው።244/3 ካልሆነ ለትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ከሚከለክሉት መቃወሚያዎች በቀር ሌለ መቃወሚያ ማቅረብን እንደተወው ይቆጠራሉ።
- ፍ/ቤቶች መቃወሚያን ማንሳት የሚችሉት ለትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚያግዱ ከሆኑ ብቻ ነው።ለምሳሌ የፍ/ቤቱ ስልጣን ካልሆነ፤ተከራካሪዎች ችሎታ የሌላቸው እንደሆነ

የቀጠለ.....

- በመቃወሚያው ላይ ብይን ለመስጠት ማስረጃ መስማት የሚያስፈልግ እንደሆነ ማስረጃ/ምስክር መስማት አለበት ሰበር ቅጽ 18 መ/ቁ 105867፤ ቅጽ 23 መ/ቁ 154023
- የስነስርዓት ይርጋዎችን ፍ/ቤት ማንሳት ይችላል የመሰረታዊ ሀግጋት ይርጋን ባለጉዳዮቹ ካለነሱ በቀር ፍ/ቤት በራሱ ለማንሳት አይችልም፤ ቅጽ 1 መ/ቁ 17361 ፍ/ብ/ሀ/ቁ 1856
- ስልጣን በሌለው የዳኝነት አካል ሲከራከሩ መቆየት ይርጋን ያቋርጠዋል ቅጽ 9 መ/ቁ 36730
- ተከሳሾች ከአንድ በላይ ከሆኑና መብታቸው የማይነጣጠል (indispensable) ከሆነ አንደኛው የሚያነሳው መቃወሚያ ለሌለው ተከራካሪም ያገለግላል። መብታቸው የተነጣጠለ ከሆነ ግን አያገለግልም ቅጽ 14 መ/ቁ 80703
- መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ የሚቀጥል ሙግት ተገቢ አይደለም ቅጽ 12 መ/ቁ 59294

የክርክሩን ጭብጥ ስለመያዝ

- በመቃወሚያው ላይ በብይን ከተዘጋ ክርክሩ ያከትማል። በተለይ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም ተብሎ ከተዘጋ ዳኝነት የተከፈለው ሊመለስ ይገባል።245/4
- መዝገቡ ካልተዘጋ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተከራካሪዎቹ የተለያዩበትን ነጥብ ለማጣራት ጭብጥ ይያዛል ፍ/ስ/246 ጭብጦቹ ክርክር የሚደረግባቸውና በማስረጃ የሚረጋገጡ ናቸው።
- ለጭብጥ አመሰራረት በክስ በግልጽ ያልተጠየቀ ዳኝነት ሊነሳ አይቻልም።ቅጽ 15 መ/ቁ 86510
- ጭብጥ ከአቤቱታዎች፤ከክስ መስማቱና ማስረጃዎች በመነሳት ሊመሰረት ይቻላል ፍ/ስ/ 248፤249

የቀጠለ.....

- ጭብጥ የሀግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ወይም ሁለቱም በአንድነት ሊሆን ይችላል።።ፍ/ስ/ 247/1/2 ጭብጥ ከአንድ በላይ ሊሆን ይችላል።።
- የሀግና የፍሬ ነገር ጭብጦች በአንድነት የሚያዙ ቢሆን በቅድሚያ በሀግ ጉዳይ ላይ ለተያዙት ጭብጦች ላይ እልባት መሰጠት አለበት 247/4
- በተቻለ መጠን ጭብጥ ማሰረጃ ከመሰማቱ በፊት መመስረትና መያዝ አለበት
- ፍርድ ቤቱ የያዘው ጭብጥ ከውሳኔ መሰጠቱ በፊት ማሻሻል፤ መቀየርና በስህተት የተያዘ ጭብጥ ለመሰረዝ ይችላል።፤ፍ/ስ/ 251
- ጭብጥን የሚይዘውና የሚመሰርተው ፍ/ቤት ነው፤ሆኖም ተከራካሪዎች ተጨማሪ ጭብጦች ካላቸው ሀሳባቸውን ሊጠይቃቸው ይችላል፤ተከራካሪ ወገኖችም የራሳቸውን ጭብጥ ፍ/ቤቱ እንዲይዝላቸው ለማመልከት ይችላሉ።። 252-253

ያለ ምስክር መስማት የሚሰጡ ፍርዶች

- ሁሉም የተያዙ ጭብጦች የግድ ምሰክር መሰማት ላያስፈልጋቸው ይችላል።

1/በታመነ ፍሬ ጉዳዮች ቅጽ 8 መ/ቁ 38597፤ቅጽ 19 መ/ቁ 112927

- ማመን ሲባል ኃላፊነትን ማመን የኃላፊነት መጠንን እንደማመን አያስቆጥርም፤ቅጽ 9 መ/ቁ 48632 ቅጽ 18 መ/ቁ 111599 በሌለበት ክሱ እየታየ ያለ ተከሳሽም በሌለበት በመታየቱ ብቻ እንዳመነ አያስቆጥረውም ቅጽ 14 መ/ቁ 82427
- በማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ሽያጭ ውል ክርክር ውል ማድረግን አምኖ ፎርማሊቲ አልተመዋለም ክርክር እንደታመነ ያስቆጥራል ቅጽ 13 መ/ቁ 36887

2/ተከሳሽ ያቀረበው መከላከያ በሀማ ፊት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ፍ/ስ/254

የቀጠለ.....

3/ክርክሩን ምስክር መስማት ሳያስፈልግ በሰነድ ማስረጃና ገለጭ ማስረጃ ብቻ እልባት ሊሰጠው የሚችል እንደሆነ

4/የተያዘው ጭብጥ የህግ ጉዳይ ጭብጥ ብቻ የሆነ እንደሆነ

5/ምስክር እንዲያቀርብ ሚዛናዊ ዕድል ተሠጥቶት ለማቅረብ ያልቻለ ተከራካሪ በተለይ ሙግቱን መጀመር ያለበት ተከራካሪ በተለይ ከሳሽ (ፍ/ስ 197/1 ፤ 197/5፤199/1፤249/1 ፤ቅጽ 8 መ/ቁ 38683 ቅጽ 20 መ/ቁ 114816

ክርክር ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

- 1/ተከራካሪዎች በፍ/ቤት ወይም ከፍ/ቤት ውጪ ሲታረቁ ፍ/ስ 274-278
- እርቅ በፍ/ቤት ከተመዘገበ የፍርድ ውጤት አለው። እንደፍርድ ይፈጸማል ቅጽ 20 መ/ቁ 113917 ቅጽ 13 መ/ቁ 65873 እርቅ ከተመዘገበ በጎ ላ ይሰረዝልኝ የሚል ክስ ተቀባይነት የለውም ቅጽ 24 መ/ቁ 162106 ፍ/ቤቶች ዕርቅን ማበረታታት አለባቸው። ቅጽ 9 መ/ቁ 52752፤ ቅጽ 7 መ/ቁ 27574 ፤ቅጽ 5 መ/ቁ 25912
- ተከራካሪዎች ከአንድ በላይ ከሆኑና የታረቁት ከፊሎቹ ከሆኑ በእርቁ ያልተስማሙት በዕርቁ አይገደዱም፤ክርክሩ ባልታረቁት መካከል ይቀጥላል።
- ቅጽ 19 መ/ቁ 109497፤ቅጽ 15 መ/ቁ 85873
- እርቁ መብቱን የነካበት 3ኛ ወገን ካለ በ358 መቃወም ይችላል ቅጽ 15 መ/ቁ 83582

የቀጠለ

- 2/ከሳሽ በራሱ ፈቃድ ክሱን ሲያነሳ/ሲያቋርጥ ፍ/ስ/ 278-279 ክስን በፍ/ቤት ፈቃድ እንዲሁም ያለፍ/ቤት ፈቃድ ለመተው ይችላል። ክስን መተው ይርጋን አያቋርጥም። ቅጽ 21 መ/ቁ 123123 ክሱ ካልተሰማ ዳኝነት ይመለሳል ቅጽ 13 መ/ቁ 76786 ያለ ፍ/ቤት ፈቃድ ክሱን ከተወ ድጋሚ ክስ ማቅረብ አይቸልም ቅጽ 21 መ/ቁ 116860
- በፍ/ቤት ፈቃድ የተቀዋረጠ ክስ በአዲስ መዝገብና በሚቀርብ ክስና ማስረጃ መታየት አለበት ቅጽ 24 መ/ቁ 161301
- 3/የክሱ ምክንያት ቀሪ ሲሆን ፍ/ስ/ 280 ቅጽ 6 መ/ቁ 23769፤ቅጽ 9 መ/ቁ 45371
- 4/የተከራካሪዎች መሞትና ወራሾች ሊቀጥሉት የማይችሉት ጉዳይ ሲሆን 48-56

ስለ እግድ አሰጣጥ ፍ/ስ 147-176

- የእግድ አላማ ምናልባት ከሳሹ ረቺ ቢሆን ፍርዱ እንዳይፈጸም ሊያደርጉ የሚችሉ ንብረት የማሸሽ ተግባራት በተከሳሹ እንዳይፈጸሙና ፍርዱ እንዳይፈጸም ሊያሰናክሉ የሚችሉ ተግባራትን ለመከላከል ነው። ጉዳዩ እልባት ካገኘና ፍርዱ ከተፈጸመ እግዱ ሊነሳ ይገባል ቅጽ 22 መ/ቁ 135590
- 1/ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የእስራት ትዕዛዝ 147-150 ተከሳሹ ከአገር ሊሸሽ የተዘጋጀ ከሆነ የፍርድ ሂደቱን ሊያሰናክን ይችላል ተብሎ ከታመነ፤ዋስትና ካላቀረበ ከአገር እንዳይወጣና ሊታገድና እስከ 6 ወር ድረስ ለማሰር ይቻላል።
- 2/በንብረት ማገድ ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች
- ንብረቱ ሲታገድ የ3ኛ ወገኖች መብት እንዳይነካ ጥንቃቄ ማድረግ
- ከክርክሩ ጉዳይ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ንብረት ከማደግ መጠንቀቅ
- በህዝብ፤ በመሰረተ ልማትና በአገር ጥቅም ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ማድረግ
- ከታገደ በሆላ እንደነገሩ ሁኔታ የታገደበትን ወገን አስተያየት መቀበል ፍ/ስ 157

የቀጠለ.....

* ሊታገዱና ሊከበሩ የማይችሉ ንብረቶች ላይ እግድ ትዕዛዝ ያለመስጠት ፍ/ስ 404
* የተከሳሹ ወይም የትዳር አጋሩ ወይም ንብረት ለማሸሽ ሲባል በህጻን ልጁ ስም የተላለፉ ንብረቶች ሊታገዱ ይችላሉ ቅጽ 11 መ/ቁ 55081
* አላግባብ በማይመለከተው ጉዳይ ንብረቱ የታገደበት 3ኛ ወገን ወይም በታገደው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ሰው የሚያቀርበውን አቤቱታ በጥንቃቄ መመርመር ፍ/ስ/ 158
* የእሽግ ትዕዛዝ ሲሰጥ ጥንቃቄ ማድረግ
* እግዱ ትዕዛዙ በሌላኛው ተከራካሪ ላይ ወይም 3ኛ ወገኖች ላይ ጉዳት ሊያድርስ ይችላል የሚባል ከሆነ ወይም በተለይም ከሳሽ ከአገር ውጪ ከሆነና በቂ ንብረት የለውም ተብሎ ሲገመት ዋስትና እንዲያስቀምጥ ማስደረግ ፍ/ስ/ 200 ቅጽ 19 መ/ቁ 110150
* እግድ ከክስ በፊትም ሊቀርብ ይችላል፤ ፍ/ቤትን ክስ ለመመስረት በቂ ጊዜ በማስፈቀድ መ/ቁ 191402 መስከረም 26/2013

ልዩ ስነስርዓቶች

* ከጉዳዩ ባህርይ የተነሳ በልዩ ስነስርዓት የሚመሩ ጉዳዮች በስነስሰረዓት ህጋችን ተካተዋል። ባመዛኙ ተከሳሹ መከላከያ ሊያቀርብባቸው የማይችሉ ጉዳዮችን የተመለከቱ ናቸው
* እንዚህ ስነስርዓቶች አስገዳጅ ሳይሆኑ ለከሳሹ ምርጫ የሚሰጡ ናቸው።
* የመከላከል መብት የተገደበና የተወሰነ ነው።ነገር ግን ህገመንግስታዊ መብትን የጠበቀ ሊሆን ይገባል ቅጽ 22 መ/ቁ 131498
* 1/ **አጭር ስነስርዓት** 284-292 ንግድ ህግ 717
* የቼክ ክስ ላይ መከላከያ ማስፈቀጃው ተቀባይነት ካገኘ በመደበኛው ስነስርዓት መመራትና ሙሉ የሙግት ሂደት መከናወን አለበት ቅጽ 20 መ/ቁ 103478፤ በአጭር ስነስርዓትም ተከሳሽ ካመነ ወይም የሸሸት ክርክር ከተከራከረ ባመነው መሰረት ፍርድ መስጠት ይቻላል ቅጽ 20 መ/ቁ 121387
* ቅጽ 16 መ/ቁ 90434 ቅጽ 12 መ/ቁ 24435 ፤ 55077፤ ቅጽ 9 መ/ቁ 43315 ፤ ቅጽ 7 መ/ቁ 20232 ለቼኩ መሰጠት ምክንያት የሆነውን ግላዊ ጉዳይ ፤የቼኩን ይዘትና መስፈርቶች እንዲሁም ቼኩ የተገኘበትን አግባብ መመርመር አለባቸው
* ቼክ ብድርን አያስረዳም ቅጽ 21 መ/ቁ 123984
* **2/የተፋጠነ ስነስርዓት** 301-314
* **3/ኃላፊነትን የማውረድ ክስ** 293-300

ክርክር መስማት እና ምስክሮችን ስለመመርመር

- ክርክር መስማት ከክስ መስማት የሚለየው ተከራካሪዎች በተያዘው ጭብጥ ላይ ሙግታቸውን ያቀርባሉ፤ምስክሮቻቸውንም አቅርበው ያሰማሉ።
- ተከራካሪዎቹ በዋናነት ፍ/ቤቱም በሁለተኛ ደረጃ ምስክሮችን ይመረምራሉ
- በቀረበው ክስና ማስረጃ ተመስርቶ ፍ/ቤቱ ፍርድ ይሰጣል።257-273
- ምስክሮች የፍትህ አይንና ጆሮ ናቸው።ምስክርነት ግዴታ ነው።ሁሉም ሰው ፍትህን የማገዝ ግዴታ አለባቸው።
- መመስከር የማይገደዱት የህግ ከለላ (immunity)የተሰጣቸው ካሉ የመንግስት ከፍተኛ አመራሮች፤አለምአቀፍ ዲፕሎማቶች፤ጥብቅ የሙያ ምስጢራዊ ግንኙነት ያላቸው ፍ/ብ/ህ/ቁ 24፤በፍርድ የተከለከሉ ወ/ህ/ቁ 123

የቀጠለ.....

- መወያያ..በሽምግልና/አስታራቂነት ስለጉዳዩ የሚያውቅ ሰው በምስክርነት እንዲመሰክር ይገደዳል?
- መወያያ..በራስ ጉዳይ ምስክር ሆኖ መቅረብ ይቻላል/ባለጋራውንስ በምስክርነት መቁጠር ይቻላል? ፍ/ስ 261
- በተለይም ባለጋራውን ቀርቦ መጎለ ፊጽሞ ቃሉን ይሰጥልኝ ለማለት ይቻላል ? ፍ/ብ/ሀ/ቁ 2002፤2026 ፍ/ስ/ 65፤57፤77
- በህግ የተለየ የምስክር ቁጥር ካልተመለከተ በቀር የምስክር ቁጥር ገደብ የለም።
- በምስክር መስማት ዕለተ ቀጠሮ ማቅረብ የሚቻለው በከሳሽ ክስና በተከሳሽ መልስ ላይ ስማቸውን የተዘረዘሩና የተቆጠሩት ምስክሮች ብቻ ናቸው።

የቀጠለ.....

- ያልተቆጠረ ምስክር ለማቅረብ አይቻልም፤ምስክር ለመለወጥ የፈለገ ወገን አስቀድሞ ለፍ/ቤቱ በመጎላ ቃል ምስክሮቹን ለመለወጥ የፈለገበትን በቂ ምክንያት በማቅረብ ፍ/ቤቱ ምክንያቱ በቂ መሆኑን ካመነበት ለተለወጡት ምስክሮች መጥሪያ ወጪ እንዲደረግ ለማዘዝ ይቻላል።ቅጽ 9 መ/ቁ 45984
- የዓይን/ቀጥታ ምስክር ለመሆን በህጉ የተቀመጠ ገደብ የለም።የዕድሜ ገደብም የለም።ዋናው እምነት ሊጣልበት የሚችል፤ቃለ መጎላ ለመፈጸም የሚችል፤ ማስታወስና ማገናዘብ የሚችል መሆኑ በቂ ነው።ምስክርነታቸውም ያዩትን የሰሙትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያውቁትን ጉዳይ እንጂ እንደ ባለሙያ አስተያየት እንዲያቀርቡ አይደለም።
- መወያያ...የህጻናትን ቃለ መጎላ መፈጸም ያለመቻል በተለይ ከ 9 ዓመት በታች ያሉት ሀሰተኛ ምስክርነት ቢሰጡ የወንጀል ኃላፊነት የሌለባቸው በመሆኑ ምስክርነታቸው እንዴት ይታያል ?

የቀጠለ.....

* የባለሙያ ምስክር (expert) ግን በተያዘው ጉዳይ ላይ ስለፍሬ ጉዳዩ ባለው ዕውቀትና ስልጠና የሰራ ልምድ የትምህርት ደረጃ መሰረት በማድረግ ሙያዊ አስተያየቱንእንዲያቀርብ ማድረግ ነው።
* የባለሙያ ምስክር በተያዘው ጉዳይ ላይ ምርመራ/ማጣራት አድርጎ ውጤቱን እንዲልክና ማብራሪያ እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል፤፤የፍ/ስ/ 136
* ለምሳሌ...መሀንዲስ፤አዲተር፤ሀኪም፤ስነልቦናባለሙያ ግብርና ባለሙያ፤.....

ምስክሮችን ስለመጥራት 111-121

የተከራካሪዎች ምስክሮች በተቻለ መጠን በአንድ ቀን እንዲቀርቡ መጥሪያ መታዘዝ አለበት።ያለመጥሪያ ምስክሮቼን አቀርባለሁ ለማለት ይችላል።111

በተቻለ መጠን የምስክሮቹን ወጪና አበል በፍ/ቤቱ እንዲያስይዙ ቢደረግ የተሻለ ነው።ፍ/ስ/ 112-114 ካልሆነም ፍ/ቤቱ ምስክሩን የጠራውን ወገን ንብረት በማስከበር ወጪው እንዲተካለት ለማዘዝ ይችላል።

መወያያ፡በድኃ ደንብ አቤቱታውን ለከፈተ ከሳሽ የምስክሮችን ወጪ ለመሸፈን የማይችል ከሆነስ መፍትሄው ምንድን ነው ?

መወያያ፤በፍ/ቤቱ ለተጠሩ ምስክሮች በተለይም የባለሙያ ምስክሮች ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት የማነው ? ፍ/ስ/ 264/2

የምስክር መጥሪያ ሙሉ መረጃ መያዝ አለበት፤የት ፍ/ቤት፤የት ችሎት፤ሰዓቱን በዝርዝር መያዝ አለበት።

የቀጠለ.....

- ምስክሮችን ለተከሳሽ መጥሪያ በሚደርሰው መልኩ መድረስ አለበት ፤ካልሆነ በቀበሌ/ገበሬ ማህበር/ፖሊስ/አሰሪው በኩል እንዲደርሰው ለማድረግ ጥረት መደረግ አለበት።
- ምስክር መጥሪያ ደርሶት የቀረ እንደሆነ ወይም መጥሪያ እንዳይደርሰው እየተሰወረ መሆኑ በመታላ ቃል ተደግፎ የቀረበ እንደሆነ ተገዶ/ታስሮ እንዲቀርብ ይደረጋል።ፍ/ስ/ 118-121፤267 ቅጽ 23 መ/ቁ 133610 ማስቀረብ ፍጹም ካልተቻለ በሌላ ማስረጃ ለ፣!ጣራት ጥረት መደረግ አለበት
- ምስክሮች በቀነ ቀጠሮው ተማልተው ያልቀረቡ እንደሆነ ያልቀረቡበትን ምክንያት በማጣራት በባለጉዳዩ ቸልተኝነት ከሆነ መብቱን ማለፍ ነው።ፍ/ስ 199
- በቂ ምክንያት ካለ ኪሳራ እንዲቆርጡ በማስደረግ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት አለበት።

የቀጠለ.....

- ምስክር ለፍትህ እርዳታ ለመስጠት እምቢተኛ ከሆነ በወንጀል ያስጠይቀዋል። ፍ/ቤቱ በወንጀል ህግ 448 መሰረት መቅጣት ይችላል።
- ምስክሮች በተቻለ መጠን በአንድ ቀን ሰምቶ መጨረስ አለበት።ነገር ግን ካልተቻለ በአዳሪ ቀጠሮ እየሰጠ ሰምቶ መጠናቀቅ አለበት።ፍ/ስ/ 197/3
- በሚዛናዊ ተለወጭ ቀጠሮ ምስክሮቹን ለማቅረብ ያልቻለ ባለጉዳይ ከሆነ ፍ/ቤቱ የቀረቡትን ምስክሮች ቃል ብቻ ለመስማት ማዘዝ ይችላል።
- ምስክር በተቻለ መጠን በችሎት ቀርቦ ሊሰማ ይገባል።261/3/ ነገር ግን በልዩና አሳሳቢ አስቸኩዋይ ሁኔታ ሲያጋጥም ቀጠሮ ተሰብሮ ተከራካሪዎቹ እንዲቀርቡ ተደርጎ ምስክር ሊሰማ ይቻላል።ሊቀርቡ ያልቻሉም ቢሆን ምስክሩን ቃሉን በችሎት ወይም ምስክሩ ባለበት ቦታ በራሱ ወይም በምትክ ዳኛ የምስክሩን ቃል ለመቀበል ይቻላል።ፍ/ስ 265 ፤122-135
- ምስክሮች ቀርበው ባለጉዳዮቹ ባይቀርቡስ/እንዳቸው ወይም ሁሉም ?

ሙግት መጀምርና ምስክር መስማት

- ክስ መክፈትና ሙግትን የመጀመርእንዲሁም የማስረዳት ሸክም በዋናነት የከሳሽ ነው።ፍ/ብ/ሀ/ቁ 2001 ፍ/ስ/ 257/258 ነገር ግን ተከሰሽ ክሱን አምኖ ሀግን ወይም ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግትን የሚጀምረው ተከሳሽ ይሆናል።ቅጽ 20 መ/ቁ 114816
- ሙግቱን የሚጀምረው ወገን ቃሉን ከሰጠ በኋላ ምስክሮቹ የሚያስረዱለትን ነጥብና ጭብጥ ያስመዘግባል፤ ሌለኛው ወገንም በተመሳሳይ ያስመዘግባል።ፍ/ስ 259 ቅጽ 9 መ/ቁ 44634 የአንዱ ወገን ምስክር የማይሰማ ከሆነ በግልጽ ምክንያቱን በማስፈር መመዝገብ አለበት ቅጽ 16 መ/ቁ 95026
- ምስክሮች ከመመስከራቸው በፊት ቃለ መኃላ ሊፈጽሙ ይገባል።ፍ/ስ 261
- ቋንቋ አስተርጓሚ በተመሳሳይ ቃለ መኃላ መፈጸም አለበት።ፍ/ስ/ 262
- ምሰክሮች ሲመሰክሩ ስለ አጠቃላይ መረጃዎቻቸው ይጠየቃሉ ፍ/ስ/269

የቀጠለ.....

በተቻለ መጠን በግልጽ ችሎት ማስቻል የተሻለ ነው። ፍ/ስ/ 263/3

- ምስክሩን የጠራው ወገን ዋና ጥያቄ በመጠየቅ ምስክርነቱን ያሰማል።በተያዘው ጭብጥ በተወሰነ መልኩ ይመሰክራል።መሪ ጥያቄ መጠየቅ አይፈቀድለትም። ፍ/ስ/ 263(1)(2)ምስክሩን መልስ መንገር አይቻልም፤፤
- ዳኞች በተለይ እውነቱን ለማውጣት፤ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም እና የምስክሮቹን ሰብዕና እንዳይጎዳ ለመከላከል ዋና ጥያቄውን መግራትና መቆጣጠር አለባቸው።
- መሪ ጥያቄ ፍ/ቤቱ በተለየ ሁኔታ ሊፈቅድ የሚችለው ምሰክሩ አስጠቂ ምስክር ሲሆን፤የረሳን ምሰክር ለማስታወስ፤ለህጻናትና ለጃጁ ፤አዕምሮቸው ውሱንነት ላለባቸው፤ስለ መረጃ ብቻ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

የቀጠለ.....

- ዋና ጥያቄ እንዳበቃ ተቃራኒው ወገን መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፣ ፤መሪ ጥያቄ ለመጠየቅም ይችላል፣፤263/3/
- የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማ ምስክሩ የሰጠውን ቃል ማስተባበል፤ምሰክሩ ሀሰተኛና ርስ በርሱ የሚጋጭ ምስክርነት መሆኑን ማሳየት፤ምሰክሩ እምነት የማይጣልበት መሆኑን ማሳየት ይቻላል።በዋና ጥያቄ ያልመሰከረውን አዲስ ጥያቄ ማንሳት አይቻልም።
- መስቀለኛ ጥያቄ ካበቃ ምስክሩን የጠራው ወገን ድጋሚ ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላል።ዓላማውም በመስቀለኛ ጥያቄ የፈረሰበትን ነገር ለማቃናት ነው። ነገር ግን አዲስ ጥያቄ አይቻልም።
- በድጋሚ ጥያቄ ምስክርን መምራት (መሪ ጥያቄ መጠየቅ) ይቻላል?

የፍ/ቤቱ ስልጣን

* ባለጉዳዮቹ የጋራ ምስክር በሚኖራቸው ጊዜ ፍ/ቤቱ የሚከተለው ስነስርዓት እንዴት ነው?
* የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በሚኖርበት ጊዜ ምስክር የመስማቱ ቅደም ተከተል እንዴት ይሆናል ?
* ዳኞች የማጣሪያ ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ።ፍ/ስ 261/4፤ 264
* የማጣሪያ ጥያቄ ሲጠየቅ አንዱን ወገን በወገነ መልኩ በሚመስል ሁኔታ መሆን የለበትም።ገለልተኛ በሆነ መልኩ መሆን አለበት፣፤
* የማጣሪያ ጥያቄው የተከራካሪ ወገኖችን ዝግጅት በማያውክና ጥያቄዎቻቸውን በማያደናቅፍ መልኩ መሆን አለበት።
* ፍ/ቤት ምሰክሮቹን በድጋሚ ሊያስጠራ ይችላል።ፍ/ስ/ 266 በራሱ ሌሎች ምሰክሮችን አስቀርቦ ሊሰማ ይችላል፣፤
* ፍ/ቤቱ በክርክሩ ቦታ በራሱ ወይም በምትክ ዳኛ ተገኝቶ መመልከት ይችላል፣፤ ፍ/ስ/ 272

የቀጠለ.....

- ፍ/ቤቱ ምስክር በሚሰማበት ወቅት በጥያቄ አቀራረብ ላይ መቃወሚያዎች እያቀረቡ ከሆነ መቃወሚያ እየቀረረበበት ያለውን ጥያቄና አስተያየት መዝግቦ የሚሰተውን ብይን ይመዘግባል። ፍ/ስ/ 270
- ምስክር ቀርቦ ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ፍ/ቤቱ ምስክርነት ለመስጠት ያልፈለገበትን ምክንያት ከጠየቀውና አጣርቶ ምክር በመስጠት እምቢተኛ መሆንና ግልጽ ሀሰተኛ ቃል መስጠት በወንጀል እንደሚያስቀጣው ካስረዳው በሁዋላ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለ ወዲያውኑ ይፈርድበታል፡፤ ወ/ህ/ቁ 442 ፍ/ስ 480/481
- ምስክሩ በራሱ ፈቃድ ቃሉን ካስተካከለ ወይም ካነሳው ቅጣቱን በማንሳት በተግሳጽ ሊያልፈው ይችላል፡፤ወ/ህ/ቁ 448

ስለ ፍርድና ውሳኔ አሰጣጥ 273፤180-191

* የማስረጃ ማሰማት ስርዓት ካለቀ በኋላ ተከራካሪ ወገኖች የሙግት መዝጊያ /ማጠቃለያ ቃላቸውን ይሰጣሉ፡፡ ፍ/ስ/ 273፤259
* ፍ/ቤቱም ፍርደና ውሳኔ ይሰጣል፡፡ፍርድ ሲጸፍ ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች አሉ፡፡
* 1/ያልተጠየቀ ዳኝነት መስጠት አግባብ አይደለም፤፤ፍ/ስ/ 182/2 ቅጽ 8 መ/ቁ 33945 ቅጽ 6 መ/ቁ 31547፤28802፤30956
* 2/ፍርድን በህግ መሰረት እንጂ በህገልቡና መስጠት ተገቢ አይደለም፡፤
* 3/በግልጽ ዳኝነት የተጠየቀባቸውን ነጥቦች በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ግልጽ ፍርድ መስጠት/በዝምታ ማለፍ እንደመከልከል ይቆጠራል ቅጽ 8 መ/ቁ 39114

የቀጠለ.....

* 4/በእያንዳንዱ ጭብጥ ላይ ተጠቃሎ ውሳኔ ለመስጠት የማይቻል ካልሆነ ነጣጥሎ ፍረድ መስጠት 182/4
* 5/ፍርዱን በግልጽ እና በተመጠነ ሁኔታ መጻፍ/ፍርዱን በጣም የረዘመ እንዳይሆን፤ረዣዥም አረፍተ ነገሮችን የማይጠቀም፤በጠጣር ቃላት ያልተመላ፤የሀጉን ድንጋጌ እንዳለ ቃል በቃል የማይጠቀም፤ጥናታዊ ጽሁፍ ሳይመስል የተጻፈ
* 6/በጣምም ያላጠረ፤ የተከራካሪዎችን ክስና መልስ አሳጥሮ ዋና ዋና ሀሳቦችን የያዘ፤ በክስ መስማት በተለየ ያየስመዘገቡት ቃል ካለ ማስፈር፤የታለፉ መቃወሚያዎች ካሉ ብይን የተሰጠበትን ቀንና ብይኑን ማመላከት፤ጭብጦችን ማስፈር፤ፍሬጉዳዩን ማስረጃውንና ህጉን በማዋሃድና በመተንነተን የፍርድ ሀተታውን መጻፍ ውሳኔና ትእዛዝ መጻፍ፤ ከተቀዋማት በትዕዛዝ የሚመጣ ምላሽ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር ተገናዝቦ እንጂ ብቸኛ ማስረጃ ተደርጎ ፍርድ መስጠት ተገቢ አይደለም ሰበር ቅጽ 24 መ/ቁ 169522

የቀጠለ.....

* 7/ጭብጡን ለማንጠር የሰማቸው ማስረጃዎች ምንነት ማስረጃዎቹ የተመዘኑበት አግባብ፤አንዱ ማስረጃ ከሌላው ሚዛን የደፋበት አግባብ፤ ፍርዱ የተመሰረተበት ህግ በግልጽ እና የተመረጠበት አግባብ በቅደምተከተል ማስፈርና የሚተቸውን ማስረጃ መተቸት
* 8/ትክክለኛውን ጭብጥ መስርቶ በፍርዱ በግልጽ ማመላከት
* 9/የተያዘው ጭብጥ ለቀረበው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው መሆን
* 10/ለየትኛው ወገን እንደተፈረደ ግልጽ ማድረግ
* 11/ወጥነት ያለውና በፍ/ቤቱ የስራ ቋንቋ መጻፍ ባዕድ ቋንቋ ያለመጠቀም ነገሮችን ግልጽ ለማድረግ ካልሆነ በቀር
* **12/ፍርዱንና ውሳኔውን ለይቶ ማመልከት**
* **13/ከጉዳዩ ባለፈ የተከራካሪዎችን ምስክሮችን ሰብዕና የሚነኩ ወገንተኝነትን ከሚያመለክቱ አገላለጾችና የሀተታ ትችቶች መጠንቀቅ**

የቀጠለ.....

* ምህጻረ ቃልን በአግባቡ መጠቀም፤ ስሞችን ቦታዎችን ፤ምሳሌያዊ/ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ማስወገድ፤ ወጥነት ያለው የቃላት አጠቃቀም፤የፊደል ግድፈቶችን በአግባቡ መልቀም፤
* ስርዝ ድልዝ ማስወገድ
* ለጉዳዩ ተዛማጅነት የሌለውን አንቀጽ ያለመጠቀም
* ወጪና ኪሳራ ተጠይቆ ከሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ዝርዝር የማቅረብ መብት መጠበቅ ወይም በቁርጥ መወሰን ወይም የየራሳቸውን እንዲችሉ መወሰን 462-466

ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድን ስለማረም

* ፍርድ በ4 መንገድ ሊታረም ይችላል፤ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት፤በይግባኝ በሰበር እና በህገመንግስታዊ ጉዳዮች ላይ ከሆነ ፌዴሬሽን ምክር ቤት
* ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት በጠባብና በተለዩ ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር አንድ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መልሶ መነካካት ስነስርዓታዊ አይደልም።
* ፍርዱን በሰጠው ፍርድ ቤት ፍርድ ሊታረም የሚችለው በ 4 ሁኔታዎች ብቻ ነው
* 1/ከስነ ስርዓት ውጪ የተፈጸሙ የስነስርዓት ግድፈቶች ለማረም 207-211 ቅጽ 1 መ/ቁ 17352፤ ቅጽ 9 መ/ቁ 44931፤ ቅጽ 8 መ/ቁ 37303 ቅጽ 16 መ/ቁ 95649 የጽኅፈት ስህተት የስነርዓት ግድፈት

የቀጠለ....

* 2/ በፍ/ስ 78 መሰረት ለተከሳሽ መጥሪያ በአግባቡ ሳይደርሰው ወይም በበቂ ምክንያት ለክስ መስማቱ ባለመቅረቡ በሌለበት የተሠጠ ፍረድ ሲነሳ
* 3/በፍ/ስ/ 6 መሰረት ዳግም ዳኝነት ጥያቄ ሲቀርብ ወንጀል ጠቀስ ማስረጃ መነሻ ፍርድ ተሰጥቶ እንደሆነ ነው።በተለይም በሀሰተኛ ምስክርነት የተሰጠ ውሳኔ፤ በሀሰተኛ ማስረጃ/ፎርጅድ ውሳኔ ከተሰጠ፤ በጉቦ በምልጃ በተሳሳተ ማስረጃ የተወሰነ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ይህ የታወቀው ከፍርድ በሁዋላ ከሆነ/በክርክሩ ወቅት ያልታወቀ፤ይህ ማስረጃ ፍርዱን ለመቀየር የሚያስችል መነሻ ሲኖር፤ይህ የተጭበረበረበረ ማስረጃ በታወቀ በ 1 ወር ጊዜ ውስጥ ከቀረበ፤አዲስ ዳኝነት እንዲከፍል በማስደረግ ፍርድ እንደገና ሊታይ ይችላል።
* አዲስ ማስረጃ አገኘሁ በሚል ብቻ ዳግም ዳኝነት ለመጠየቅ አይቻልም።
* በሀሰተኛ ማስረጃ ፍርድ ከተሰጠ አዲስ ክስ በማቅረብ ሳይሆን በቀድሞው መዝገብ ዳግም ዳኝነት በመመልከት ማረም ነው። ቅጽ 24 መ/ቁ 166205

የቀጠለ...

- ዳግም ዳኝነት ለመጠየቅ እስከ ሰበር ሄዶ የጸና ቢሆንም በድጋሚ ማየትን አይከለክልም።ቅጽ 9 መ/ቁ 43821
- ዳግም ዳኝነት አይታይም ወይም ይታያል ተብሎ በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ለማለት አይቻልም። ፍ/ስ/ 6/4 ነገር ግን ድጋሚ ከታየ በሁዋላ በሚሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ መጠየቅን አይከለክልም።
- ዳግም ዳኝነት ሲጠየቅ በመደበኛው ስነስርዓት ይመራል።
- ሰበሮች ቅጽ 9 መ/ቁ 42871፤45839፤ቅጽ 15 መ/ቁ 91968፤93137 ፤42501 ቅጽ 6 መ/ቁ 08751
- 3/ <u>ፍርድን ስለመቃወም **358-360/41/418/421/455**</u>
- <u>**358 እና 418 ዓለማና አፈጻጸም ልዩነትና አንድነት ላይ እንወያይበት**</u>

የቀጠለ....

* በአንድ ፍርድ በተሰጠ ውሳኔ ከመፈጸሙ በፊት ፍርዱ መብቱን የሚነካበት 3ኛ ወገን ፍርዱን ለመቃወም ይችላል።
* ይህ ተከራካሪ ፍርዱ መብቱን እንዴት እንደነካበትና ፍርዱ ባለበት ቢፈጸም መብቱን የሚነካበት መሆኑን በአቤቱታው በመሃላ ማመልከት አለበት።
* በተለይም በአቤቱታው ክርክር ሲደረግ ከፍርድ በፊት ያልሰማና የማያውቅ የነበረ መሆኑን እንጂ ክርክር መኖሩን እያወቀ መብቱ እንደሚነካበት እያወቀ በወቅቱ ጣልቃ ለመግባት ሲችል ውጤቱን ጠብቆ አቤቱታ ካቀረበ መቀበል የለብንም። ቅጽ 12 መ/ቁ 56795 ፤ ቅጽ 25 መ/ቁ 181236 ጣልቃ ልግባ ብሎ ውድቅ ተደርጎበት ከሆነም መልሶ በ 358 መቃወም አይችልም።ቅጽ 9 መ/ቁ 40229
* ዳኝነት መክፈል አለበት።
* ለቀደመው ፍርድ ከተነሳና የክርክሩ አካል እንዲሆን ከተደረገ በሁዋላ መደበኛው ስነስርዓት ይፈጸማል።ቅጽ 15 መ/ቁ 86133 ቅጽ 16 መ/ቁ 86398
* ማስረጃ የመስጠት ውጤት ብቻ ያላቸውን ውሳኔ መቃወም አስገዳጅ አይደለም ማስረጃውን ህጋዊነት ከሚመለከት በቀር ቅጽ 15 መ/ቁ 82679 ፤79871 ቅጽ 24 መ/ቁ 161650

የቀጠለ.....

- መቃወሚያ የሚቀርበው ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት እንጂ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አይደለም ቅጽ 20 መ/ቁ 115892
- መቃወሚያ የቀረበበት ፍርድ የተሸረ እንደሆነ የመቃወም አቤቱታው አስፈላጊ አይሆንም ቅጽ 23 መ/ቁ 148270
- አንድ በክርክር ተሳታፊ ያልነበረ ሰው መብቱን የነካበትን ፍርድ የሰጠው የሰበር ችሎት በሆነ ጊዜ በፍ/ስ/ 358 መሰረት መቃወሚያ ማቅረብ ሳይሆን አዲስ ክስ በመመስረት መጠየቅ ያለበት ስለመሆኑ ማለትም በ358 ቀጥታ ለሰበር የሚቀርብ አቤቱታ ስነስርዓታዊ አይደለም ቅጽ 19 መ/ቁ 102056 ቅጽ 13 መ/ቁ 31264
- በፍ/ስ 358 ሆነ 418 የመቃወም አቤቱታ ለመምራት የሰነድ ማስረጃ ስላልቀረበ መብት የለም ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ ቅጽ 17 መ/ቁ 97094

የቀጠለ....

* ፍ/ስ 358
* ፍርዱን መቃወም ነው
* ባልተሳተፍኩበት የተሰጠ ፍርድ ግን መብቴን የነካ ስለሆነ ይነሳልኝ ነው።
* መቃወሚያው የሚቀርበው ፍርድ ባረፈበት ዋናው መዝገብ ላይ ነው።
* ቅጽ 12 መ/ቁ 53607፤42714፤ 55842፤ ፤ ቅጽ 17 መ/ቁ 97094
* ፍርዱ ከተፈጸመ በሁዋላ ካወቀ በአዲስ ክስ ከሶ ይጠይቅ ፍ/ስ/ 421 እና 455 ቅጽ 12 መ/ቁ 50835 53421 ቅጽ 9 መ/ቁ 37214
* ፍ/ስ 418
* የተፈረደብኝ ፍርድ ሳይኖር ባለዕዳ ሳልሆን ንብረቴ የቀዳሚነት መብት ያለበት ንብረት ለፍርድ አፈጻጸም ሊከበርብኝ አይገባም የሚል መቃወሚያ ነው
* አፈጻጸሙን መቃወም ነው
* ፍርዱ ላይ ሳይሆን የአፈጻጸም መዝገቡ ላይ የተሰጠውን የንብረት ይከበር ትዕዛዝ መቃወም ነው።
* ቅጽ 13 መ/ቁ 67127፤ቅጽ 13 መ/ቁ 31264
* መደበኛው ስነስርዓት ይከተላል
* ቅጽ 15 መ/ቁ 86133

የይግባኝ ስነስርዓት ፍ/ስ 320-349

- ይግባኝ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ስለሚፈተሹ ቅድመ ሁኔታዎች
- 1/ይግባኝ መብት ስለመሆኑ አዋጅ 1234/13 አንቀጽ 54
- በግልጽ በህግ ወይም ተከራካሪ ወገኖች ይግባኝ የማለት መብታቸውን ካለስቀሩ በቀር በተሰጠ ፍርድ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኝ የማለት መብት አለው፤፤ በፍቺ ውሳኔ ላይ የፍቺ ውሳኔውን በተመለከተ ብቻ ይግባኝ ለማለት አይቻልም፡፡ ሌሎች ህግጋት ፍ/ብ/ህ/ቁ 2152/2153 ፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 6/4፤326/3፤306፤466፤ 350/351 ቅጽ 18 መ/ቁ 98593፤የስራ ክርክር ጉዳይ ከከፍተኛው ፍ/ቤት አልፎ በጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ሊታይ አይችልም፡፡
- በታመነ ፍሬ ጉዳይ ላይ በተሰጠ ፍርድ እንዲሁም በእርቅ በተዘጋ ጉዳይ ላይ ይግባኝ መቅረብ የለበትም፡፡

የቀጠለ.....

- **2/ይግባኝ ለማለት መብት ያለው ሰው ማነው?320/1**
- በፍርዱ ላይ በከፊልም ሆነ በሙሉ ቅሬታ ላይ ያለው በስር ፍ/ቤት በከሳሽነት በተከሳሽነት በጣልቃገብነት ፍ/ስ 41 በ3ኛ ወገን ተከሳሽነት ፍ/ስ 43 እግድ እንዲነሳለት በመጠየቅ ፍ/ስ/ 158 ቅጽ 21 መ/ቁ 123833 በተተኪ ከሳሽ/ተከሳሽነት ፍ/ስ 39/40 በአፈጻጸም ሀራጅ ገዢነት ባጠቃላይ በስር ፍ/ቤት መዝገብ የተሳተፈ ተከራካሪ ወገን እንጂ አዲስ ባለጉዳይን አይጨምርም
- መወያያ፡በስር ፍ/ቤት በሌለበት ውሳኔ የተሰጠበት ተከሳሽ ባልተከራከረበት መዝገብ ላይ ቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል ወይም በሌለበት የተባለው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ውድቅ ተደርጎበት ከሆነስ?
- መልስ ሰጪውም ይግባኝ በተባለበት መዝገብ ላይ የራሱን ይግባኝ ካለው ሌላ መዝገብ መክፈት ሳያስገድደው በዚያው መዝገብ መስቀለኛ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል። ፍ/ስ 340
- የራሱን ይግባኝ ካቀረበ ወይም ይግባኝ በተለያየ መዝገብ ከተከፈተ ሊጣመሩ ይገባል ቅጽ 24 መ/ቁ 165616

የቀጠለ.....

- 3/ይግባኝ ለማየት ስልጣን ስላለው ፍ/ቤት
- ፍርዱን ከሰጠው ፍ/ቤት በመቀጠል ላለው ፍ/ቤት /የዳኝነት አካል ነው።
- 4/በሰር ፍ/ቤት አስቀድሞ ለመታረም የሚችሉበት ተህግ አግባብ ካለ አምዋጦ ማቅረብ ፍ/ስ/ 320/2/ 6፤78፤358፤207-211
- 5/ሁለት ጊዜ ይግባኝ የሌለ ስለመሆኑ ፍ/ስ/ 321
- የይግባኝ ዕድል አንድ ጊዜ ብቻ ነው።ይግባኝ ብሎ የጸናበት ወገን መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለው የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ከሚያቀርብ በቀር በድጋሚ የሚያቀርበው ይግባኝ የህግ ተቀባይነት የለውም።
- ለምሳሌ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ወገን ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔውን የሚያጸናው ቢሆን መልሶ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ አይቻልም፣ ፤ ነገር ግን ውሳኔው ቢሻር ወይም በከፊል ቢሻሻል የተሸረበት ወገን በቀጣይ ይግባኙን ለመመልከት ስልጣን ወዳለው ፍ/ቤት ይግባኙን ለማቅረብ ይችላል።

የቀጠለ.....

- 6/ይግባኝ የሚባለው በመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በሁዋላ ስለመሆኑ/ጊዜያዊ ውጤት ባላቸው ጥቃቅን ትእዛዝ እና ብይኖች ላይ የመጨረሻው ፍርድ ሲሰጥ ካልሆነ በቀር ይግባኝ ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ ፍ/ስ 320(3)ቅጽ 6 መ/ቁ 19142 ቅጽ 19 መ/ቁ 116209 ነገር ግን እግድ ይነሳልኝ ብሎ 3ኛ ወገን በፍ/ስ/ አመልክቶ እግዱ አይነሳም ከተባለ ዋናው መዝገብ ላይ ተከራካሪ ባለመሆኑ ፍርዱን ሳይጠብቅ በትዕዛዙ/ብይኑ ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል።ቅጽ 17 መ/ቁ 101632
- በጊዜያዊ ውጤት ባለው ትእዛዝ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ሳይጠብቁ ይግባኝ ለማለት የሚቻለው ከፍርድ በፊት የእስራት ትዕዛዝ ወይም የንብረት ማስለቀቅ ትዕዛዝ የተሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው።፤ፍ/ስ/ 320/4 ቅጽ 15 መ/ቁ 89893
- የድህነት አቤቱታው ውድቅ የተደረገበት ከሳሽ ይግባኝ ለማለት ይችላል ቅጽ 6 መ/ቁ 23744

የቀጠለ.....

- **7/ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ፍ/ስ/ 323-326**
- **የፍትሀብሄር ይግባኝ ፍርዱ በተሰጠ በ 60 ቀናት፤ ሰራ ክርክር በ 30 ቀናት የመጨረሻው ቀን ዝግ ቀን ከሆነ በቀጣዩ ስራ ቀን መስተናገድ ይችላል ቅጽ 23 መ/ቁ 152845**
- **ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ካለፈበት ይግባኙን ከማስፈቀጃ ጋር ማቅረብ ይኖርበታል፤ ያለፈበትን በቂ ምክንያት/እክል በመጋለ ቃል ተደግፎ ማስፈቀጃ መቅረብ አለበት። ቅጽ 25 መ/ቁ 184388 ፍ/ቤቱ ማስፈቀጃውን ለመልስ ሰጪው አስተያየቱን እንዲያቀርብ ይልክለታል።በቂ ምክንያት ከሆነ ይግባኙን ይከፍትለታል።፤ ፍ/ስ 326 ቅጽ 12 መ/ቁ 59085 ቅጽ 13 መ/ቁ 74785 ቅጽ 8 መ/ቁ 38145**
- **በቂ ምክንያቶች ውሳኔ ግልባጭ በፍ/ቤቱ ችግር ከዘገየበት፤ህመም፤ ሀዘን፤ መታሰር፤መውለድ፤አገራዊ ግዳጅ ላይ መሆን ነገር ጠበቃዬ /ነገረፈጂ/ወኪሌ ረስቶት ነው ጊዜው ያለፈው በቂ ምክንያት አይደለም። ቅጽ 12 መ/ቁ 57360**

የቀጠለ.....

- 8/የይግባኝ ዋና ዋና ቅሬታዎች ፍ/ስ/ 327-329

በይግባኝ በዋናነት መቅረብ ያለባቸው ቅሬታዎች

- የእኩልነት መብት ያለመከበር ግልጽ አድሎ የነበረ መሆኑን መመርመር /ተከራካሪዎቹን በእኩልነት ያለማስተናገድ ቅጽ 6 መ/ቁ 25026፤ ቅጽ 8 መ/ቁ 37761
- የስነስርዓት ግድፈቶች
- ፍሬ ጉዳይ መሳት/ያለመረዳት/መምታታት
- የማስረጃ ምዘና ስህተት
- የህግ ትርጉም ስህተት/አግባብነት የሌለው /ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት የሌለው ህግን መጠቀም/ህግን አዛብቶ መተርጎም

ይግባኝ ሲመረመር

የሰር ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ/ውሳኔ ለመስጠት እንዴት እንደቻለ

* የክርክር አመራሩ የስነስርዓት ህጉን የተከተለ/ያከበረ ስለመሆኑ
* ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ጭብጥ ስለመያዙ
* ጭብጡን ለመወሰን የቀረቡ ማስረጃዎች አግባብነት ያላቸው ስለመሆናቸው
* ማስረጃዎች በተመዋላ ሁኔታ ስለመሰማታቸው
* ማስረጃዎች በአግባቡ ስለመመዘናቸው እና ይህንንም በፍርድ ሀተታው ስለመመልከቱ
* በፍሬ ነገር ረገድ የተደረሰው ድምዳሜ አግባብነት እና ከህግ ጋር የተገናዘበበት ሁኔታ
* የተጠቀሰው ህግ ለተያዘው ጉዳይ አወሳሰን ስላለው አግባብነት ማጣራት

የቀጠለ.....

- 9/ በይግባኝ ላይ አዲስ ክርክር/ሙግት/አዲስ ማስረጃ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ...ፍ/ስ 328፤329፤345፤346
- ይግባኝ በስር ፍ/ቤት ተከራካሪዎች አቅርበውት በነበረው ፍሬ ጉዳይና ሙግት ላይ የተገደበ ነው።።ምንም አይነት አዲስ ክርክር አዲስ ፍሬነገር አዲስ ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም።።
- ይግባኝ እንደገና ማስረጃ መስማት አይደለም።።ነገር ግን በስር ፍ/ቤት ቀርቦ በስር ፍ/ቤት ያለበቂ ምክንያት አልቀበልም ያለው ማስረጃ ከሆነና ለትክክለኛ ፍትህ አስፈላጊ የሆነን ማስረጃ ፍ/ቤቱ በፍ/ስ 345 መሰረት አቤቱታ ከይግባኙ ጋር ከቀረበለት በቂ ምክንያት መሆኑን ከተቀበለ ተቃራኒው ወገን አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ ማስረጃውን ለመቀበል ላለመቀበል መወሰን ይችላል።።ፍ/ቤቱ በጠባብ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል ቅጽ 22 መ/ቁ 137831፤ ቅጽ 8 መ/ቁ 29861፤ ቅጽ 2 መ/ቁ 29861፤ቅጽ 9 መ/ቁ 39853፤ቅጽ 15 መ/ቁ 72980 ለማጣራት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ምስክሮችንም አስቀርቦ ለማጣራት ይችላል።። ማስረጃዎችንም ማስቀረብ ይችላል።። ቅጽ 21 መ/ቁ 99474

የቀጠለ.....

- ይግባኙ አቤቱታ ሲቀርብ ፍ/ቤቱ ሬጅስትረር ስነስርዓቱን ተከትሎ የቀረበ አቤቱታ መሆን አለመሆኑን ካጣራ በሁዋላ ዳኝነት በደንቡ መሰረት በስር ፍ/ቤት የተከፈለውን ዳኝነት መጠን በግማሽ በማስከፈል ወይም በድኃ ደንብ በቀረበ አቤቱታ ከሆነም ተያይዞ ለችሎት ይቀርባል።ቅጽ 20 መ/ቁ 117754
- የስር ፍ/ቤት መዝገብ ተያይዞ ወይም ተገልብጦ እንዲቀርብ ይደረጋል። ይግባኙ ሲመረመር ሊጣራ የሚገባው ምንም አይነት የህግም ሆነ የፍሬ ጉዳይ የማስረጃ ግድፈት ካልተገኘበት መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ ይግባኙን በፍ/ስ 337 መሰረት በመሰረዝ መዝገቡ ይዘጋል።
- ሊጣሩ የሚገባቸው የቅሬታ ነጥቦች ካሉ በመለየትና በመዝገቡ በማስፈር ይግባኙን ያስቀርባል በማለት መጥሪያ ለመልስ ሰጪው ለክርክር ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ይታዘዛል።

የቀጠለ.....

መወያያ፡ ይግባኝ ላይ መልስ እና የመልስ መልስ የሚቀርብበት ስነስርዓት እንዴት ይታያል?
ፍ/ስ 338/339

10/ይግባኝ መጥሪያ ፍ/ስ 69-78

ይግባኙን ለመስማት በተቀጠረ ቀን ግራ ቀኙ ካልቀረቡ እንዲሁም ይግባኝ ባዩ ቀርቶ መልስ ሰጪው ቀርቦ ይግባኙን ሙሉ ለሙሉ ክዶ ከተከራከረ ይግባኙ ይሰረዛል። ባንጻሩ መልስ ሰጪው መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ መሆኑ ከተረጋገጠ በሌለበት ይግባኙ ይሰማል፤መዝገቡ ግራቀኙ ሳይቀርቡ ተዘግቶ የሚንቀሳቀስ ከሆነ መልስሰጪው በድጋሚ ሊጠራ ይገባል ቅጽ 24 መ/ቁ 169407

11/የሰር ፍ/ቤትን ፍርድ/አፈጻጸም ስለማገድ ፍ/ስ/ 332-336

ፍ/ቤቱ ይግባኙን መርምሮ የመጨረሻ ፍርድ እስከሚሰጥበት ድረስ ይግባኝ ባይ በአፈጻጸም እየተገደደ መሆኑን ወይም መልስ ሰጪው በፍርዱ እየተገለገለበት ከሆነ ይህም ሊካስ የማይቻል ጉዳት የሚያደርስበት መሆኑን በመሃላ ቃል አስደግፎ ካቀረበ ፍረዱን ለማገድ ይቻላል።

የቀጠለ.....

- ነገር ግን የእግድ ትዕዛዝ ሲሰጥ ይግባኝ ባዩ የተፈረደበትን ገንዘብ እንዲያስቀምጥ ወይም ዋስትና እንዲያስቀምጥ ለማዘዝ ይቻላል። ፍ/ስ 336
- የፍ/ቤት ፕሬዝደንት ለ 15 ቀን ፍርዱን ከመፈጸም ለማገድ ይችላል። ፍ/ስ 334
- 12/የይግባኝ ክርክር ውጤት ፍ/ስ 348፤341-343
- መሻር ነገር ግን ሲሻር በዝርዝር የተሸሩት ነጠቦች ተብራርተው ሊሆን ይገባል ቅጽ 16 መ/ቁ 92903 ፤ ማጽናት፤ በከፊል ማሻሻል፤በመመሪያ ጭብጥ መስርቶ ለስር ፍ/ቤት በድጋሚ አጣርቶ እንዲወስን መመለስ በመቃወሚያ የተዘጋ መዝገብ መቃወሚያውን ከሻረው መመለስ የግድ ነው ቅጽ 24 መ/ቁ 163166 የተመለሰለት ፍ/ቤትም በተሰጠው መመሪያ መሰረት ድጋሚ ሙግቱን መምራት አለበትቅጽ 13 መ/ቁ 72189 ቅጽ 24 መ/ቁ 166617 ይህ ማለት ግን በዘፈቀደ ማስረጃ ይሰማል ማለት ሳይሆን በስነስርዓቱ አግባብ ብቻ ነው ቅጽ 17 መ/ቁ 97217

የቀጠለ....

- **ይግባኝ ላይ በፍ/ቤቶች አሰራር ላይ የሚታዩ ችግሮች**
- **ይግባኞችን ባግባቡ ሳይመረምሩ አያስቀርብም እያሉ መሰረዝ**
- **ይግባኙን የሚጣሩትን ነጥቦች ሳይለዩ በደፈናው ያስቀርባል ማለት**
- **ይግባኙ ፍርዱ ቢለወጥ ነገር ግን የማይነጣጠል መብት ባላቸው ሰዎች ሲሆን ይግባኝ ባላሉት ሰዎችም ተፈጻሚ ነው ፍ/ስ/ 331 ቅጽ 22 መ/ቁ 139138**

- ✓ **ተገቢ የሆነ የስነስርዓት ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ጉዳዮችን ወደ ስር ፍ/ቤት መመለስ**
- ✓ **ምክንያት/ውጤት የሌለው የእግድ ትዕዛዝ መስጠት**
- ✓ **በመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ይግባኙን ለመመርመርና ለማጣራት ያስቀርባል ከተባለበትና ከተከራከሩበት ነጥብ ውጪ ወይም በተጨማሪ ፍረድ መስጠት**
- ✓ **ከስር ፍ/ቤት የባሰ ውሳኔ መስጠት /መፍትሄ የማይሰጥ ውሳኔ መሆን**
- ✓ **ክርክሩን ከስር ፍ/ቤት ክርክር የበለጠ ረጅም ጊዜ የሚፈጅና የፈጀ መሆን**
- ✓ **በተለይ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሲሽር በደፈናው ተሻረ ከማለት ውጪ የተሻረበትን አግባብ ሳያብራሩና ሳይተነትኑ ሳይተቹ መወሰን**

የፍትሀብሄር ፍርድ አፈጻጸም 371-455

* አፈጻጸም የሚነሳው ከተሰጠ ፍርድ በመሆኑ ፍርዱንና ውሳኔውን በመለየት ግልጽ በሆነ መልኩ ለአፈጻጸም ምቹ በማድረግ የሚፈጸመውን ክፍል ለይቶ በውሳኔ ማስፈር ያስፈልጋል።ይህም አፈጻጸሙን ቀላል ያደርገዋል።
* ፍርድ ከተሰጠ በሁዋላ መዝገብን አፍኖ ያለማስቀመጥና በፍጥነት ተጽፎ ለተከራካሪዎች እንዲሰጥ ማደረግ
* በአፈጻጸም የ 3ኛ ወገኖች መብት እንዳይነካ ጥንቃቄ ማድረግ 3ኛ ወገኖች አቤቱታ ሲያቀርቡም በጥንቃቄ መመርመር 418 ንብረቱ ተሸጦ ካለቀ በሁዋላ ለመቅረብ አይችልም። ፍ/ስ/ 444/445
* የፍርድ ባለዕዳን ከተፈረደበት በላይ ንብረቱን ያለማገድ
* ከስነስርዓቱ ውጪ ፍርድ ባለዕዳን ያለማሰር
* ንብረቶች እንዲታገዱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ቸል በማለት ንብረቶች እንዲሸሹ ማድረግ

የቀጠለ.....

ፍርድ ሲፈጸም ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት ወይም ከበላይ ፍ/ቤት በስር ፍ/ቤት ፍርዱን እንዲያስፈጽም በመመሪያ ተላልፎለት ከሆነ ለተመራለት ፍ/ቤት የአፈጻጸም አቤቱታው መቅረብ አለበት፡፡ 371-374

ንብረቱ በሌላ ግዛት ከሆነ በሌላ ክልል እንዲፈጸም በውክልና ማስተላለፍ አለበት፡፡

ውጪ ሀገር የተሰጠ ፍርድም ፍ/ስ 456፤458 እስካመ□ላ ድረስ የተለየ ቃልኪዳን ስምምነት ባይኖርም ሊፈጸም ይችላል ቅጽ 24 መ/ቁ 161597

የግልግል ዳኞች ውሳኔም ቴምብር ቀረጥ ከተከፈለበት ቦነ□ላ በፍ/ቤት ሊፈጸም ይችላል፡፡

- ✓ አፈጻጸም መጠየቅ የሚችለው የፍርድ ባለመብቱ ወይም ወራሹቹ ወይም ባለመብቱ መብቱን ያስተላለፈላቸው ሰዎች ናቸው፡፤
- ✓ የፍርድ ባለዕዳው ከሞተ ከወራሾቹ ወይም ከዋሶቹ ፍርዱን እንዲፈጽሙ ለመጠየቅ ይቻላል፡፡
- ✓ አፈጻጸም የሚጠየቀው ፍርዱ በተሰጠ በ 10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ስራ ክርክር ከሆነ 1 ዓመት ውስጥ ነው፡፡ ቅጽ 11 መ/ቁ 53527፤ ቅጽ 9 መ/ቁ 50148 ቅጽ 8 መ/ቁ 35018

የቀጠለ.....

- ፍርድ የሚፈጸመው እንደ ፍርዱ ብቻ ነው። ከፍርዱ ውጪ መጨመር መለወጥ አይቻልም። ቅጽ 7 መ/ቁ 22448 ቅጽ 2 መ/ቁ 16720 ቅጽ 9 መ/ቁ 50148 አፈጻጸም ችሎት ድጋሚ ክርክር ለማድረግም ሆነ ፍርደን መሻር ስልጣን የለውም።ቅጽ 19 መ/ቁ 103787፤ ቅጽ 18 መ/ቁ 96814 ቅጽ 13 መ/ቁ 69471፤ ቅጽ 8 መ/ቁ 38041፤ ቅጽ 7 መ/ቁ 28019፤ቅጽ 6 መ/ቁ 29949
- የ3ኛ ወገን መብትና ጥቅም ላይ መቃወሚያ በፍ/ስ 418-420 ካልቀረበበት በቀር አፈጻጸም ላይ የሚደረግ ክርክር አይኖርም።ቅጽ 17 መ/ቁ 90722፤ ቅጽ 13 መ/ቁ 69385 ቅጽ 11 መ/ቁ 48997 ቅጽ 10 መ/ቁ 46143 ቅጽ 8 መ/ቁ 32143 ቅጽ 7 መ/ቁ 25031፤29653፤23989፤28154
- መወያያ....ፍርስ ፍርድ የሚለው ጽንሰሀሳብ ቅጽ 18 መ/ቁ 101345 ቅጽ 17 መ/ቁ 98541 ፍርስ ፍርድ ሊፈጸም አይችልም ቅጽ 17 መ/ቁ 95587

የፍርድ ባለዕዳውን ስለመመርመር

- ፍርድ ቤቱ ባለዐዳውን ፍርዱን የማይፈጽምበትን ምክንያት ይጠይቀዋል ፍ/ስ 386/2 አዲስ ክርክር ፍርዱ ስህተት ነው የሚል ግን አይደለም።
- በቂ ምክንያት ካልሰጠ ፍርዱ እንዲፈጸም ያስገድዳል።ንብረት እንዲከበር ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል።386/3፤ 392(1)(3)
- ሆነ ብሎ ለመፈጸም እምቢተኛ ከሆነ ንብረት ካሸሸ ማሰር ይቻላል። 386/4 እና 387-391 ከ 6 ወር በላይ ግን ሊታሰር አይቻልም።

በፍርድ ቤት ውሳኔ/ትዕዛዝ አሰጣጥ ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች

* ላለፈጸመ የሚውል ንብረት ሳይጠቀስ እንደፍርዱ እንዲፈጸም እየተባለ የሚሰጥ ትዕዛዝ
* ለአፈጻጸም የሚያስቸግር ትዕዛዝ መስጠት
* ሊፈጸም የማይቻል ትዕዛዝ መስጠት ምሳሌ ባዶ መሬት ተሸጦ ይከፈሉ...
* ስለአፈጻጸሙ አግባብነት ያላቸውን ህጎች በመዘንጋት ትዕዛዝ መስጠት
* በዋናው ፍርድ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እና በአፈጻጸሙ ትዕዛዝ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ትዕዛዝ መለያየት
* የባለጉዳዮች የስም አመዘጋገብ ስህተት
* በርካታ ባለጉዳዮች ካሉ የተወሰኑትን ስም ከመዘገቡ በሁዋላ ሌሎችን አለመመዝገብ እና በአፈጻጸሙ የሚደርሳቸውን ድርሻ አለመለየት

የቀጠለ.....

* የማይንቀሳቀስ ንብረት አዋሳኞችን አለመጥቀስ ፍ/ስ/ 225
* በፍርድ ባለዕዳው የተሙዋላ ስም ሳይጠቀስ በባለዕዳው ስም ያለ ንብረት ፈልጉ የሚል ትዕዛዝ
* የሚሰጠው ትእዛዝ እና ነባራዊ ሁኔታው የማይገናኝ መሆን፤ ወይም ጥቅል ትዕዛዝ መስጠት
* የሀራጅ ድንጋጌዎችን መጣስ
* ሀራጅ ማስታወቂያ ሲወጣ ስለ ንብረቱ ያሉ ዕዳዎች ግዴታዎች ሳይጠቀሱ ማውጣት ለምሳሌ ቀረጡ ያልተከፈለ ንብረት፤ ካርታ የሌለው ይዞታ መሆን..
* ለአፈጻጸም ሚዛናዊ ጊዜ ያለመስጠት
* የአስፈጻሚ አካላት የበቂ ቦታ ያለመኖር ችግር ትዕዛዝ ለረጅም ጊዜ ማቆየት
* ሊፈጸም የማይቻል ፍርድ ከሆነ ሳይዘጉ ማቆየት ፍ/ስ 392

የፍርድ አፈጻጸም ስነስርዓት

- ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠ ፍርድ ከፍ/ስ 394-398 ባለው ስነስርዓት ይፈጸማል።ከተቻለ በአንድ ጊዜ ካልተቻለ ደግሞ በየጊዜው እንዲከፈል ለማዘዝ ይቻላል። ፍ/ስ 186 እና 386
- ገንዘቡን ካልከፈለ የባለዕዳውን ወይም በትዳር አጋሩ ስም ያለውን የጋራ ንበርት ወይም በህጻን ልጁ ስም ያደረገውን ወይም የዋሱን ንብረት በማስከበር በመሸጥ ለማስፈጸም ይቻላል።ቅጽ 11 መ/ቁ 55081
- የሚንቀሳቀስ ንብረት ለማስረከብ ወይም ለማስለቀቅ የተሰጠ ፍርድ በፈቃደኝነት ለማስረከብ እምቢተኛ ከሆነ በህግ ኃይል እንዲያስረክብ ይደረጋል። ፍ/ስ 399
- የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስረከብ/ለማስለቀቅ የተሰጠ ፍርድ ከሆነ በተመሳሳይ በፈቃዱ ወይም በመገደድ እንዲለቅ ይደረጋል።ፍ/ስ 402

የቀጠለ...

- ቤቱ የተቆለፈ ከሆነ ቁልፉን በመስበር ወይም ሌላ ማናቸውም ዘዴ በመከተል ለማስፈጸም ይቻላል።
- በአፈጻጸሙ ወቅት ሁከት ረብሻ አምባጋሮ የሚያነሳ ውሻ የሚለቅባቸው፤ጎረቤት አድማ የሚያስነሳ፤ማስፈራራት፤ በማናቸውም ሁኔታ ፍርዱ እንዳይፈጸም ለማሰናከል እና ለማወክ የሞከረ ማናቸውም ወገን የማሰር ትዕዛዝ ለፖሊስ ለመስጠት ይቻላል፡
- ፍርድ ያረፈበት ንብረት በአፈጻጸም ወቅት ከሌለ ከወደመ ሊገኝ ካልቻለ በፍርዱ ግምቱ እንዲከፈል አማራጭ ፍርድ ተሰጥቶ ከሆነ ግምቱን ማስከፈል ይቻላል። ሆኖም በፍርዱ ይህን ዓይነት አማራጭ ግምት ክፍያ ፍርድ ካልተሰጠ በአዲስ ክስ ግምቱ እንዲከፈል ማስፈረድ ይኖርበታል።
- ውል እንዲፈጸም ሰነድ እንዲፈረም የተሰጠ ትዕዛዝ በፍ/ስ 400 እና 401 መሰረት ይፈጸማል።

ንብረት ስለማስከበር ፍ/ስ 404-417

* ለፍርዱ አፈጻጸም ንብረት እንዲከበር የሚባልበት አቤቱታ ሲቀርብ ንብረቱን በዝርዝር የሚገልጽ በፍ/ስ 379 መሰረት ተሙዋልቶ መቅረብ አለበት።
* ንብረቱ በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ መሆን አለበት።ተመጣጣኝ ያልሆነ ንብረት ካላተገኘ ግን በማናቸውም ንብረት ላይ ይፈጸማል።
* ሊከበሩ የማይችሉ ንብረቶችን ማስከበር አይቻልም።ፍ/ስ/ 404 ቅርሶች፤የመንግስት ስራ ማስኬጃ በጀት፤ባዶ መሬት፤የህዝብ ንብረቶች መከበር የለባቸውም።
* በማስከበር ሂደት ቅድሚያ ጥሬ ገንዘብ፤ ውድና የከበሩ ዕቃዎች/ወርቅ...፤ ተራ የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎች፤ ልዩ ተንቀሳቃሽ ዕቃዎች ...ማሽኖች ተሽከርካሪዎች፤ አክሰዮኖች በመጨረሻም ድርጅት እና ቤቶች በቅደምተከተል ቢሄድ የተሻለ ነው።

የቀጠለ.....

- የሚከበረው ንብረት በሌላ ፍ/ቤት እግድ ቢኖርበትስ ወይም ብዙ ሰዎች የፍርድ ባለገንዘብ ቢሆኑስ ፍ/ስ 403? በዚህ ጊዜ የቀዳሚነት መብት ያለውን እንመለከታለን። በተለይም ንብረቱን ቀድሞ ያሳገደው ወገን የቀደመ መብት አለው።ቀድሞ ያሳገደ እንጂ ቀድሞ በተፈረደለት አይደለም። ቅጽ 16 መ/ቁ 97206 ቅጽ 15 መ/ቁ 88867 ቅጽ 11 መ/ቁ 40945
- በህግ ከማናቸውም ዕዳዎች በፊት የቅድሚያ መብት የተሰጣቸው ነግብር ዕዳ በተመለከተ ገቢዎች ባለስልጣን፤ ቅጽ 11 መ/ቁ 48997 የሰራተኛ ክፍያ በተመለከተ አሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 167፤ የመያዣ መብት ያላቸው ባንኮች አዋጅ 98/90
- እኩል ደረጃ ያላቸው ባለመብቶች ከሆኑ በታገደው ገንዘብ መጠን እንደድርሻቸው በመቶኛ ማቃመስ/ማከፋፈል ነው።

የሀራጅ ስነስርዓት ፍ/ስ 422-449

* መጀመሪያ ንብረቱን መነሻ ዋጋ በሚመለከተው አካል /ባለሙያ ወይም ግራቀኙ ከተስማሙ በራሳቸው ግምት ማስገመት ፍ/ስ 422
* ቅጽ 20 መ/ቁ 104943 ቅጽ 9 መ/ቁ 37503 ቅጽ 10 መ/ቁ 43858
* ሀራጅ ማስታወቂያው የተሙዋላ መረጃ ይዞ መውጣት አለበት። ፍ/ስ 423
* የሀራጅ ማስታወቂያው በህጉ አግባብ አየር ላይ መዋሉን በአግባቡ ለህዝብ እይታ ግልጽ በሆኑ ስፍራዎች መለጠፉን ማጣራት ለሚንቀሳቀስ ንብረት 15 ቀናት ለማይንቀሳቀስ ንብረት 30 ቀናት ፍ/ስ 425/426 ወይም በጋዜጣ ማስወጣት
* ባለዕዳው ከሀራጁ ቀን ድረስ ከከፈለ ሀራጁ ይቀራል። ፍ/ስ 427
* ባለመብቱና ባለዕዳው ፍ/ቤቱ ካልፈቀደላቸው በቀር በሀራጁ መሳተፍ አይችሉም። ፍ/ስ 430/431

የቀጠለ...

* በመጀመሪያው ሀራጅ ገዢ ካልተገኘ ወይም ያሸነፈው ወገን ከፍሎ ለመውሰድ ካልቻለ ወይም ሀራጁ ስነስርዓትን ካልተከተለ ሁለተኛ ሀራጅ ይታዘዛል።ፍ/ስ 428
* አሸናፊው ያስያዘው ገንዘብ ለጨረታው ወጪ መሸፈኛ ይሆናል።ኪሳራም ከደረሰ ሌዩነቱን ይከፍላል።ፍ/ስ 429
* በሁለተኛው ሀራጅ በ ዜሮ መነሻ ዋጋ ሀራጁ ለመውጣት ይቻላል።
* የሀራጁን ዋጋ ከፍሎ ለማስቀረት የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን ካለ የቅድሚያ መብቱ ይጠበቅለታል።ለሀራጅ አሸናፊውም በሀራጁ መነሻ ያወጣውን ወጪ ይተካለታል። ሆኖም ሁሉም ወገን የቅድሚያ መብት ከጠየቀ ለሀራጅ አሸናፊው ይተላለፋል። ፍ/ስ 436 እና 439
* በሀራጅ የተሸጠን ንብረት ርክክብ ማደናቀፍ በህግ ሀይል ማስረከብ ይቻላል። ፍ/ስ 450-455

ወጪና ኪሳራ አወሳሰን ፍ/ስ 462-466፤ 183/1/ሠ

- ወጪና ኪሳራ መወሰን ፍትሀን የማስከበር ጉዳይ ነው።
- ክርክር ወጪ ያስወጣል፤ ጊዜያቸውን ከመደበኛ ስራቸው ላይ ቀንሰው ክርክሩን ለመከታተል ያውሉታል።ለድካም ይዳረጋሉ።
- ያለግባብ ረቺውን ወገን ሲያንገላታ፤ ለወጪና ኪሳራ የዳረገው ተረቺ በረቺው ላይ የደረሰውን ጉዳት ለመካስ ነው።
- በደፈናው ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ተብሎ የሚሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም።አላግባብ የተጋነነም ሆነ አላግባብ ያነሰም ወጪና ኪሳራም ተገቢነት የለውም።
- ብዙውን ጊዜም ወጪና ኪሳራ ለመስጠትም ሆነ ለመከልከል የተተነተነ ምክንያት አይሰጡም

የቀጠለ.....

- ወጪና ኪሳራ መክፈል ያለበት ተረቺ ወገን እንዲከፍል ቢወሰን የተጎዳውን ወገን በመካስ ፍትህን ያሰፍናል።
- ቅን ልቦና ሳይኖራቸው ወይም ያለ በቂ ምክንያት ክስ እያቀረቡ የሚያጉላሉ ከሳሾችን ወይም በሰው ንብረትን መብት ድርቅ ብለው ለሚከራከሩ ተከሳሾች ቆም ብለው እንደሚያስቡ ያደርጋቸዋል።
- በዚህም የፍ/ቤቶች ሀብት ያላግባብ እንዳይባክን ማድረግ ይቻላል። አላስፈላጊ መዛግብት በተወሰነ ደረጃ ይቀንሳሉ።
- የወጪና ኪሳራ ዝርዝር መጠየቂያ አቤቱታ ፍርድ በተሰጠበት መዝገብ ይስተናገዳል። ቅጽ 14 መ/ቁ 83701

የቀጠለ.....

- ወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት እንዲጠበቅለት ወይም በቁርጥ እንዲወሰንለት በዋናው ክስ/ይግባኝ ሲቀርብ ወይም መልስ ሲቀርብ በግልጽ ካልተጠየቀ ወይም በክስ መስማቱ ዕለት ካላስመዘገበ በቀር ያልተጠየቀ ዳኝነት ስለሚሆን መወሰን አይቻልም።
- ወጪና ኪሳራ በዝርዝር ከነማስረጃው ቢቀርብ የተሻለ ነው።።ፍ/ስ/ 462
- ማስረጃ ሊቀርብባቸው የማይቻሉ ወጪዎች ከሆኑ ፍ/ቤቱ በርትዕ ሊወስንባቸው ይችላል። ፍ/ስ 463፤464
- ወጪና ኪሳራ ከጉዳዩ ጋር የተዛመደና ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት የወጣ ብቻ እንጂ ተዛማጅነት የሌላቸውና ግላዊ ወጪዎችን አይጨምርም። የተጋነነና ቅንጦታዊ ወጪ ከሆነ ፍ/ቤቱ ለመቀነስ ይቻለዋል። ለምሳሌ የተጋነነ የጠበቃ አበል ቅጽ 1 መ/ቁ 17191

የቀጠለ.....

- የተረታ ወገን ሁሌም ቢሆን ወጪና ኪሳራ መክፈል አለበት ማለት ሳይሆን በተለይ ቅን ልቦናን መመልከቱ ተገቢ ነው። ቅጽ 18 መ/ቁ 109055፤ ቅጽ 15 መ/ቁ 91103 የጉዳዩን ውስብስብነት፤የፈጀውን ጊዜ፤ የወጪው ተዛማጅነት፤የተጋነነ አለመሆን ከግምት መግባት አለበት።
- ረቺ ለተረቺ ግን በማናቸውም ሁኔታ ወጪና ኪሳራ ይክፈለው ተብሎ መወሰን አይቻልም። ቅጽ 11 መ/ቁ 46281፤ ቅጽ 4 መ/ቁ 22260
- ወጪ ኪሳራ ብዙውን ጊዜ የጠበቃ አበል፤የዳኝነት ክፍያ፤የቴምብር ቀረጥ ክፍያ፤የትራንስፖርት ወጪ ፤የምስክር አበል ወጪ፤የትርጉም ስራ ወጪ፤ የጽህፈት የኮፒ ወጪ፤ የታጣ ገቢ፤የመሳሰሉትን ይጨምራል።

የቀጠለ.....

- በወጪና ኪሳራ ውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይቻላል።ፍ/ስ 466 ነገር ግን በይግባኙ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ቢሻርም ቢጸናም ይግባኝ አይኖረውም።ነገር ግን ለሰበር ማቅረብን አይከለክልም። ቅጽ 18 መ/ቁ 98593
- ወጪና ኪሳራን ከወለድ ጋር እንዲከፈል ለመወሰን ይቻላል።
- ከወጪና ኪሳራው በተጨማሪ አንድ ተከራካሪ ከቅን ልቦና ውጪ የመከራከሪያ ክስ ወይም የመከላከያ ማሰረጃ ያቀረበ ተከራካሪ ለእያንዳንዱ ሀሰተኛ ማስረጃ ማስረጃ ብር 500 የማይበልጥ ካሳ ለተበዳዩ እንዲከፍል ፍ/ቤቱ ሊወስን እንደሚችል ያመለክታል።ፍ/ስ 465
- ካሳውን ሊወሰን የሚችለው ተከራካሪው ወገን በሀሰት የተከራከረውና ሀሰተኛ ማስረጃ ያቀረበው ክርክሩን ለማሰናከል፤ ጊዜ ለመፍጀት ወይም አንደኛውን ወገን ሆነ ብሎ ለመበደል ወይም ለማጉላለት ሆነ ብሎ ያደረገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው።

ፍ/ቤትንና የችሎት ስራን ስለማስከበር ፍ/ስ 480/481 ወ/ህ/ቁ 449

- የችሎት /የፍ/ቤትን ስራን የሚያውኩ የሚረብሹ የሚያሰናክሉ አድራጎቶች ጨኸትን፤ አምባጋሮን፤ጸያፍ ንግግርን፤ ለችሎቱ ተገቢ ያልሆነ ምላሽ መስጠትን፤ ችሎቱን በማይመጥኑ ቃላት ማናገርን፤ የዳኛውን ክብር መንካትን፤ድብድብን፤ ለሚዲያ ተገቢ ያልሆነ መግለጫ መስጠትን፤ የፊት ገጽታን፤ የችሎት ስርዓትን ያለማክበርን፤ ተከራካሪ ወገንን ፤ምሰክርን የችሎት ሰራተኞችን መዝለፍ፤ያልተገታ ሳቅና ለቅሶ፤ በችሎት መመገብ፤ ማስቲካ፤ አልኮል፤ ሲጋራ፤ ጫት፤ዕፅ መጠቀም ፤ህገወጥ መሳሪያ ስለቶች ይዞ መገኘት፤ የተጋነነ ሽቶ፤ ሆነ ብሎ መጥፎ ጠረንን፤ ስርዓት አልባ አለባበስ፤ ጸጉር ስራ፤ ልጆችና ህጻናት ሰብስቦ መረበሽ፤ስልክ ማስጮህ.....በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የችሎቱን የምትክ ዳኛውን ስራ፤ ባጠቃላይ የፍ/ቤቱን ስራ ማወክ ተገቢ አይደለም። ቅጽ 15 መ/ቁ 92459 ቅጽ 9 መ/ቁ 48273 ቅጽ 9 መ/ቁ 43005 ወ/ህ 451

የቀጠለ.....

- ፍ/ቤቱ የችሎት ስነስርዓትን ለማስከበር አስፈላጊ ነው ያለውን ርምጃ ችሎቱን በደፈረው ማንኛውም ሰው (ተከራካሪ ባለጉዳይ፤ ምስክር፤ ታዳሚ፤ መንገደኛ፤ የፍ/ቤቱ ሰራተኛ ላይ ሌላ ሊሆን ይችላል....) ለመውሰድ ይችላል። ፍ/ስ/ 480
- ርምጃው አስተዳደራዊ ሊሆን ይችላል።አጥፊውን መገሰጽ፤ ማረም፤መምከር፤ማስጠንቀቅ፤ ወይም ከችሎት ማስወጣት፤ ሊሆን ይችላል።ነገር ግን መሳደብ ማዋረድ ማንቀዋሸሽ እንዲሁም ሰብዓዊ መብቱንና ክብሩን የሚነካ እርምጃ መውሰድ ስህተት ነው።
- ዳኛ በግል ጉዳይ ወይም በቂም በቀል በመነሳት ችሎት መድፈር በሚል መቅጣት የለበትም።

የቀጠለ.....

- የሚወሰደው ርምጃ የዳኝነት ስራ አካሄድንና ፍ/ቤቱን ለማስከበር ብቻ የታለመ መሆን አለበት።ባለማወቅ የተፈጸመ ጥፋት ከሆነ በምክር ማለፍ የተሸለ ነው።
- ከአስተዳደራዊ ርምጃው በመቀጠል በያዘው ማናቸውም መዝገብ ላይ የገንዘብ ቅጣት እና እስራት ርምጃ ወዲያውኑ ለመውሰድ ይቻላል።ነገር ግን ጥፋተኛው ራሱን እንዲከላከል ዕድል ለመስጠት ይቻላል።ወ/ህ/ቁ 449፤451
- እስራት ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ 1 ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እስራት በከፍተኛው ፍ/ቤትና ከዚያ በላይ ከሆነ እስከ 3 ዓመት
- ችሎቱ የተደፈረው በችሎት ከሆነ መቀጮ ከሆነ ከ 3000 ብር ያልበለጠ
- ከችሎት ውጪ ከሆነ እስከ 1000 ብር ወይም እስከ 6 ወር ቀላል እስራት
- በማስገደድ ወይም የኃይል ድርጊት ካለው ተጨማሪ የወንጀል ተጠያቂነት ይኖረዋል።ወ/ህ 441

እናመሰግናለን!